# 1ኛ ተሰሎንቄ መልዕክት

# ማጥኛ

በኢትዮጵያዊያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን
የቅዱሳንን ማነጽ አገልግሎት የተዘጋጀ
2010

© Ethiopian Evangelical Baptist Church, 2010
የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን, ፳፻፪
2822 S. Jupiter Road
Garland, TX 75041
214 703 0100
www.eebc-dallas.org

## ጥናት አንድ
## የእምነት የተስፋ እና የፍቅር ውጤቶች

## የምንባብ ክፍል፡ 1ኛ ተሰሎንቄ 1:1-3

## የመሪው ማስታወሻ

1ኛ ተሰሎንቄ 1:1-3 ያለው ክፍል የመልዕክቱ መግቢያ ክፍል እንደመሆኑ መጠን፣ ሐዋሪያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ ራሱን እና ከእርሱ ጋር በአገልግሎት እየተሳተፉ ያሉትን ጠቅሶ፣ ለተሰሎንቄ ሰዎች ሰላምታ ያቀርባል (1:1)። በመቀጠልም፣ ከቁ 2-3 ባለው ሐዋሪያው በጸሎቱ ጊዜ ሁሉ ለተሰሎንቄ ሰዎች ያለውን ምስጋና ይገልጻል።

ሐዋ 17 የተሰሎንቄን ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስ እና ሲላስ እንዴት እንደጀመሩ እና በዚያ በነበረው ስደት ምክኒያት ከሦስት ሳምንት በላይ መቆየት እንዳልቻሉ ያሳየናል። ወደ ኃላ ላይ ደግሞ ጢሞቴዎስ እነዚህን በተሰሎንቄ ያሉትን አዳዲስ አማኞች ለመጎብኘት ጳውሎስ ልኮት እንዳያቸው ከዚሁ ክፍል መረዳት እንችላለን። ስለዚህ ጳውሎስ በሰላምታው ላይ ሲላስን እና ጢሞቴዎስን ሲጠቅስ ግለሰቦቹ ለተሰሎንቄ ሰዎች እንግዳ እንዳይደሉ እናውቃለን።

ወንጌል ወደ ተሰሎንቄ ከተማ በቀላሉ እንዳልገባ ከሐዋ 17 መረዳት እንችላለን። በእንደዚህ አይነቱ ቦታ ጌታን ተከትሎ መኖር አስቸጋሪ እና ብዙ ዋጋ የሚያስከፍል ነገር ነው። ሆኖም ግን ጳውሎስ በዚህ መልዕክቱ "የእግዚአብሔር አብ እና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሆኑት የተሰሎንቄ ሰዎች" [አዲሱ መደበኛ ትርጉም]፣ ማለቱ በጌታ የሆኑ ሰዎች ምንም ያህል ሰይጣን ቢገፋቸው እና አለም አንቅራ ብትተፋቸው፣ መድረሻ እና መጠጊያ ጌታ እንዳላቸው ያሳየናል።

ጳውሎስ ለእነዚህ ሰዎች ሰላምታ ሲያቀርብ፣ "ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እና ሰላም ለእናንተ ይሁን" ማለቱ በጊዜው የተለመደ የክርስቲያኖች ሰላምታ ቢሆንም ግን እጅግ ትልቅ ትርጉም ያለው ነገር ነው። ጸጋ በኃጢአት ለጠፋው ፍጡር የማይገባ የእግዚአብሔር ስጦታ ሲሆን፣ ይህ ስጦታ የሚያስፈልገን ለመዳን ብቻ ሳይሆን፣ ከድነትም በኃላ የክርስትናን ሕይወት በሚገባ ለመኖር የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገናል (ዕብ 4:16)። ስለ ሰላም ስናነሳ፣ የሰው ልጅ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስፈልገው ሰላም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መፍጠር ቢሆንም፣ ከድነትም በኃላ በእግዚአብሔር ልቡ እንዳረፈ ሰው ለመኖር የእግዚአብሔር ሰላም ያስፈልገዋል። እንግዲህ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ጸጋ እና ሰላምን ቢመኝላቸውም፣ ግን ዋነኛው የጸጋ እና የሰላም ምንጩ ግን እግዚአብሔ መሆኑን አያይዞ ያሳስባቸዋል። ከቁ 2-3 ባለው ክፍል፣ እነ ጳውሎስ በጸሎታቸው ጊዜ ሁሉ ስለተሰሎንቄ ሰዎች ምስጋናን እንደሚያቀርቡ ይገልጻል። በሐዋ 17 እንዳየነው የተሰሎንቄ ሰዎች አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ጌታን የተቀበሉ አዳዲ አማኞች እንደሆኑ ተመልክተናል። ስለዚህም እንደ ሰው መከራ ሲበዛባቸው፣ "ጌታን ትተው ወደ ኃላ ይመለሱ ይሆን?" የሚል ፍርሐት በነ ጳውሎስ ልብ ውስጥ ሊፈጠር ይችላል። ሆኖም ግን እነዚህ ሰዎች በጌታ ጸንተው መቆም ብቻ ሳይሆን፣ በእምነት፣ በፍቅር እና በተስፋ የተሞሉ ክርስቲያኖች ሆነው ተገኝተዋል - ስለዚህም ጳውሎስ ጌታን ያመሰግናል። ምንም እንኳን እምነት፣ ተስፋ እና ፍቅር የማይታዩ (abstract) እንደሆኑ ቢታሰብም፣ እነዚህ ሰዎች ግን ያላቸውን እምነት፣ ተስፋ እና ፍቅር በሚያደርጉት ነገር በግልጽ ያሳዩ ሰዎች ናቸው። ጳውሎስ በዚህ ክፍል እንደሚያሳየን የተሰሎንቄ ሰዎች እምነታቸውን በስራ እየገለጡ ያሉ ሰዎች ናቸው። በእርግጥም ደግሞ አንድ ሰው ያለውን እምነት የሚያሳየው በስራ ነው (ያዕ 2:18-26)። ለወገኖች እና ለጌታ ያላቸውን ፍቅር ደግሞ ለጌታ እና ለሰዎች በሚደክሙት ድካም እየገለጡ ነው። ፍቅራቸው የአንደበት ብቻ ሳይሆን በግልጽ በተግባር የሚታይ ነው። እንዲሁም ደግሞ በጌታ ያላቸውን ተስፋ በጽናታቸው እየግለጡ ነው ያሉት። ጌታ አንድ ቀን እንደሚመጣ እና ከዚህ አለም እንደሚገላግላቸው ተስፋ በማድረግ፣ በጊዜው እያለፉ ባሉበት መከራ ውስጥ ጸንተው ቆመዋል።

እንግዲህ በዛሬው ጥናታችን የምንመለከተው፣ የዛሬውን የንባብ ክፍል በመንተራስ እውነተኛ እና ክርቲያናዊ የሆነ እምነት፣ ተስፋ እና ፍቅር ካለን፣ በሕይወታችን የሚያመጡትን ባሕሪያቶች እንመለከታለን። ከዚህም ባሻገር በጌታ ያለንን እምነት፣ ለጌታ እና ለወገኖች ሊኖረን የሚገባውን ፍቅር እንዲሁም በጌታ ሊኖረን ስለሚገባው ተስፋ በመመልከት ሕይወታችንን በእነዚህ አቅጣጫዎች እንዴት ማሳደግ እንዳለብን እንመለከታለን።

የጥናቱ አላማ፡- በጌታ ያለንን እምነት፣ ለጌታ እና ለወገኖች ሊኖረን የሚገባውን ፍቅር እንዲሁም በጌታ ላይ ልናደርገው ስለሚገባን ተስፋ እንዴት ማሳደግ እንዳለብን መረዳት።

መግቢያ፡- ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንጦስ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ እንዳሰፈረው፣ አንድ ቀን ጌታ ሲገለጥ፣ አለን የምንለው ምድራዊ ነገርም ሆነ ዛሬ የምናገለግልበት የጸጋ ስጦታ ሁሉ አልፎ የሚቀሩት ነገሮች፣ እምነት ተስፋ እና ፍቅር እንደሆኑ ገልጿል (1ኛ ቆሮ 13:13)። ይህ እውነት ከምንም ነገር ሁሉ በላይ በመጀመሪያ ልንጠማው የሚገባን ነገር፣ በሕይወታችን እምነት ተስፋ እና ፍቅር እንዲሞላ መሆን እንዳለበት ያሳስበናል። የዛሬው የጥናት ክፍል፣ እምነት ተስፋ እና ፍቅር በሕይወታችን ሲሞላ በእኛ ውስጥ የሚታየውን ባሕርይ በመመልከት፣ እምነት ተስፋ እና ፍቅር እንዳለው አማኝ እንዴት መመላለስ እንዳለብን እናያለን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. መልዕክቱ የተጻፈው ከማን ነው?

    - የመልዕክቱ ተቀባዮች መልዕክቱን የጻፈውን ሰው እና አብረውት ያሉትን ሰዎች ያውቃሉ ብለህ ታስባለህ?
    - እንደሚተዋወቁ ምን ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል?

2. መልዕክቱ የተጻፈው ለማን ነው?

    - ጸሐፊው የመልዕክቱን ተቀባዮች "በእግዚአብሔር አብ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ሐረግ ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚነግርህ ምንድን ነው?

3. ከቁ 2-3 ባለው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ያለውን ሰላምታ ያቀርባል። ጳውሎስ በሰላምታው ከእግዚአብሔር እና ከክርስቶስ ኢየሱስ ሰላም እና ጸጋ እንዲበዛላቸው ይባርካቸዋል።

    - በዚህ  መሰረት ጸጋ ምንድን ነው?
    - ሰው የሚድነው በጸጋ ከሆነ ለዳኑ ሰዎች ጸጋን መመኘት ለምን ያስፈልጋል?
    - ሰላምስ ክርስቲያኖች የሚያገኙት እንዴት ነው?

4. ከሰላምታው በመቀጠል ጳውሎስ ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች የሚያቀርበውን ምስጋና ይገልጻል።

    - ለጳውሎስ የምስጋናው ምክኒያት ምንድን ነው?

5. እምነት ፍቅር እና ተስፋ ምንድን ናቸው? ልዩነታቸውስ ምንድን ነው?

6. በቁ. 3 ላይ የተሰሎንቄ ሰዎች ባላቸው ተስፋ ምክኒያት በክርስትናቸው እንደጸኑ ይነግረናል።

    - የተሰሎንቄ ሰዎች ተስፋ የሚያደርጉት ምንድን ነው?
    - የእግዚአብሔር ቃል በ1ኛ ጢሞ 6:17 ላይ በምን ተስፋ እንድናደርግ ነው የሚመከረን?
    - በክርስቶስ ኢየሱስ እና በሚመጣው የዘለአለም ሕይወት ተስፋ ማድረጋችን የሚታወቀው በምንድን ነው?

7. ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ብርቱ እምነት እንዳለው የሚታወቀው በምንድን ነው?

- በእምነት እና በስራ መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

8. በቁ. 3 ላይ "የፍቅራችሁ ድካም" ሲል ምን ማለቱ ነው?

    - በዚህስ ክፍል መሰረት ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች የፍቅር ሰዎች መሆናቸውን በምን አወቀ?

    - በዚሁ መሰረት ጌታን እና ሰዎችን የምንወድ ከሆነ፣ ፍቅራችን የሚታወቀው በምንድን ነው?

9. በ1ኛ ቆሮ 13:13 ላይ በጌታ መገለጥ ጊዜ፣ የጸጋ ስጦታ የሚባሉት ሁሉ ሲቆሙ እምነት ተስፍ እና ፍቅር ግን ጸንተው እንደሚኖሩ እና ካሉን ነገሮች እና ስጦታዎች ሁሉ በላይ አስፈላጊ እንደሆኑ ያስገነዝበናል።

    - እምነት፣ ተስፋ እና ፍቅር ለክርስቲያን በጣም አስፈላጊ እንዲሆኑ እና ከጸጋ ስጦታዎች ሁሉ በላይ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?
    - ዛሬ እንደ ክርስቲያን አንተ/አንቺ በእምነት የበረታ፣ ፍቅር የበዛለት እንዲሁም ክርስቶስን ተስፋ በማድረግ የሚጸና ብርቱ የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን ማድረግ ያለብህ/ሽ ምንድን ነው?

መደምደሚያ:- የተሰሎንቄ ሰዎች አዲስ አማኞች ከመሆናቸው ሌላ ብዙ በብዙ መከራ የሚያልፉ ቢሆኑም፣ በክርስቶስ ባላቸው እምነት፣ ለጌታ እና ለወገኖች ባላቸው ፍቅር፣ እንዲሁም በጌታ ተስፋ በማድረግ በመከራ የሚጸኑ የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው። ከዚህም ሁሉ በላይ እነዚህ ባሕርያት ጌታ በጣም እንዲኖረን ከሚፈልጋቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል ናቸው። ስለዚህም በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚያምን ሰው በመልካም ስራ ልንተጋ፣ ለክርስቶስ እና ለወገኖች ፍቅር እንዳለው ሰው፣ አንዳችን ሌላችንን የምንረዳ ልንሆን እንዲሁም በሁለመናችን በክርስቶስ ተስፋ አድርገን በሁሉ ልንጸና ይገባናል።

## ጥናት ሁለት

## ወንጌል በአማኝ ውስጥ የሚተክላቸው እውነቶች - እምነት ፍቅር እና ተስፋ

### የምንባብ ክፍል፡ 1 ተሰ 1፡4-10

### የአስተማሪው ማስታወሻ

ባለፈው ጥናታችን፣ የ 1ኛ ተሰሎንቄን መግቢያ ስንመለከት፣ ጸሐፊው ጳውሎስ እንደሆነ፣ የመልዕክቱ ተቀባዮች የተሰሎንቄ ሰዎች እንደሆኑ አይተናል። በማያያዝም ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች ባላቸው እምነት የሚያደርጉትን ስራ፣ ባላቸው ፍቅ ምክኒያት ለሌሎች የሚደከሙትን ድካም እንዲሁም በጌታ ባላቸው ተስፋ ምክኒያት ያተረፉትን ጽናት ተመልክተናል። ከዚህም እውነት በመነሳት እውነተኛ እምነት መልካም ስራን እንደሚያስከትል፣ እውነተኛ ፍቅር ለሌሎች በመድከም የሚገለጥ እንደሆነ፣ በጌታም የሚደረግ እውነተኛ ተስፋ ጽናትን እንደሚያመጣ ተመልክተን ነበር። በ1ኛ ተሰ 1:4-10 ባለው የዛሬው ጥናታችን ደግሞ፣ ሰው በወንጌል እውነት ሲለወጥ፣ እምነት ተስፋ እና ፍቅር አብረው የሚመጡ እውነቶች እንደሆኑ እናያለን። በቁ. 4 ላይ እነ ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች በእግዚአብሔ እንደተመረጡ ማወቃቸውን ይናገራል። ከቁ 5-10 የተሰሎንቄ ሰዎች መመረጣቸውን እርግጠኞች እንዲሆኑ ያስቻላቸውን ነገሮች ዘርዝሮ ይናገራል። በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች እንዲሁ እንደ ተራ ነገር አልመጣም፣ ነገር ግን በቁ 5 ላይ እንደምናየው ከእግዚአብሔር ኃይል እንዲሁም ከነጳውሎስ ጥሩ የሕይወት ምሳሌ ጋር ነበር። ወንጌል በእንደዚህ አይነት መልኩ ወደ እነሱ ሲመጣ፣ አማኞቹ ቃሉን በብዙ ደስታ ከመቀበል ሌላ ጌታን በመምሰል መመላለስ ጀመሩ (ቁ. 6)፣ እምነታቸው በሌላ ቦታ ሁሉ እስኪሰማ ድረስ ለሌሎ እንኳን ምሳሌ ሆኑ (7-8)። ከዚህም በላይ ይህ ወንጌል ከቁ 9-10 እንደምናየው፣ የእግዚአብሔርን ቃል ያሰሟቸውን አገልጋዮች የሚቀበሉበትን <u>ፍቅር</u>፣ ወደፊት ከጥፋት ሊያድናቸው የሚመጣውን ጌታ የሚጠባበቁበትን <u>ተስፋ</u> እንዲሁም እውነተኛው አምላክ ሕያው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን አውቀው ከባዕድ አምልኮ የሚመለሱበትን <u>እምነት</u> አመጣ (9-10)።

ቁ. 4 ከቁ. 3 የጀመረውን አሳብ በመቀጠል፣ እነጳውሎስ የነዚህን ሰዎች የእምነት ስራ፣ የፍቅር ድካም እንዲሁም የተስፋ ጽናት ሲያስቡ እዲያመሰግኑ የሚያደርጋቸው ነገር የተሰሎንቄ ሰዎች በእግዚአብሔር መመረጣቸውን ማወቃቸው ነው። ስለዚህም በእምነት የምንሰራው፣ በፍቅር የምንደክመው እና በተስፋ የምንጸናው፣ በእግዚአብሔር እንድንመረር አይደለም - ገና ድነትን ሳይቀበሉ መልካም የሚያደርጉ እና በፍቅር የሚሰሩ ሊኖሩ ይችላሉ እና። ነገር ግን እነዚህን ሁሉ የምናደርገው ስለተመረጥን ነው። የተሰሎንቄ ሰዎችም በእምነት የሚሰሩት፣ በፍቅር የሚደከሙት እና በተስፋ የሚጸኑት ስለተመረጡ ነው። በቁ 5 ጸሐፊው የተሰሎንቄ ሰዎች እንደተመረጡ ያወቁት፣ ወንጌል ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች በኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስ እና በብዙ መረዳት በመድረሱ መሆኑን ይገልጻል። <u>ኃይል</u>፣ የመጣው ወንጌል ከተራ ቃል ያለፈ እና ሰውን መለወጥ የሚችል መሆኑን ሲያሳየን፣ <u>መንፈስ ቅዱስ</u> ደግሞ ቃሉ የሚሰብኩት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ቃሉን በመተርጎም እና በልባቸው እንዲገባ በማድረግ አብሮ የሚሰብከው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ያሳስበናል። ከዚህም በላይ እነ ጳውሎስም ቃሉን ይሰብኩ የነበረው <u>በብዙ መረዳት</u> ነበር። ስለዚህም የሚናገሩትን ወንጌል በሚገባ ከማስተዋላቸው ሌላ ሰሚዎቹን እንደሚለውጥ በሚገባ ተረድተዋል።

ከቁ. 6-7 ባለው ወንጌል በዚህ አይነት መልኩ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች መምጣቱ ያስከተለውን ነገር ይገልጽልናል። በወንጌል ምክኒያት <u>ብዙ መከራ</u> ቢደርስባቸውም ይህንን እውነት <u>በመንፈስ ቅዱስ ደስታ</u> ተቀብለውታል። በዚህም ከነ ጳውሎስ ያዩትን ሕይወት በመከተል እነ ጳውሎስን እና ጌታን መሰሉ ቁ. 7። ምንም እንኳ ጌታን ባያዩትም፣ የሰሙትን ብቻ ተቀብለው መኖራቸው በሰሙት ቃል ብቻ መርካታቸውን ከዚህ እንማራለን።

ቁ. 8 የተሰሎንቄ ሰዎች ይህንን ወንጌል ከሰሙ በኃላ በእነሱ ብቻ አልቀረም ነገር ግን የሰሙትን እና የዳኑበትን ወንጌል ለሊሎችም ሰበኩ። የሰበኩት ግን ወንጌሉን ብቻ ሳይሆን የራሳቸውንም ምስክርነት ነበር። ስለዚህ የሚሰሟቸው ሰዎች ሃይማኖትን ሳይሆን የሰውን ሕይወት የሚለውጥ የምስራች እንደሆነ ይረዳሉ። ከቁ 9-10 በዚህ ቁጥር ላይ ወንጌልን ከሰሙ በኃላ በሕይወታቸው ስለመጣው እና ሌሎች ስለሰሙት ለውጥ እንማራለን።

አንደኛ ፍቅራቸውን ያገለገሏቸውን ሰዎች በመቀበል እና በማገልገል ገለጹ። ወደ እናንተ መግባታችን የሚለው እነ ጳውሎስ ራሳቸውን በመቀበል ማስተናገዳቸውን ያሳያል።

ሁለተኛ ተስፋቸው ከሚመጣ ቁጣ የሚያድናቸውን ጌታ መጠባበቅ ሆነ።

ሦስተኛ እምነታቸው እግዚአብሔር ሕያው እና እውነተኛ አምላክ መሆኑን ተረድተው ከጣዖት ወደ እርሱ በመዞር  እሱን ለማገልገል (ለመታዘዝ) ውሳኔ እንዲወስኑ አስቻላቸው።

የጥናቱ ዓላማ:- ሁላችንም የምስጋናችን ርዕስ ስላለን እምነት፤ ፍቅር እና ተስፋ እንዲሆንና በነዚህም ይበልጥ ለማደግ

እንነድንጸልይ ለማነሳሳት

መግቢያ:- ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በሚጸልይላቸው ጊዜ ሁሉ ስላላቸው እምነት፤ ፍቅርና ተስፋ እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግን የሚያስተምር ክፍል ነው። በተጨማሪም ክፍሉ እነጳውሎስ ወንጌልን ለተሰሎንቄ ሰዎች ሲሰብኩ ስላሳዩት ምሳሌአዊ አኗኗራቸውና የተሰሎንቄም ሰዎች ይህንንም ምሳለነት እንዴት እነደተከተሉ እነሱም ለሌሎች እንዴት ምሳሌ እንደሆኑ ያስተምራል።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1. የእነጳውሎስ የጸሎትና የምስጋና ርዕስ ምንድን ነው?

   1.1 እምነትና ስራ ትርጉማቸውንና ዝምድናቸውን አስረዳ

   1.2 ፍቅርና ድካም ትርጉማቸውንና ዝምድናቸውን አስረዳ

   1.3 ተስፋና ፅናት ትርጉማቸውንና ዝምድናቸውን አስረዳ

"ሳናቋርጥ" "ሁል ጊዜ" የሚሉት ቃላት እነጳውሎስ ስለሚያመሰግኑበትና ስለሚጸልዩበት ጉዳይ ምን ያስተምራል? ስለነጳውሎስስ ምን ይናገራል?

እነጳውሎስ ሁል ጊዜ ያለማቋረጥ መጸለያቸውንና ማመስገናቸውን ሲሰሙ የተሰሎንቄ ሰዎች ምን የሚማሩ ይመስልሃል? (Hint: እነሱምየጸሎትነ የምስጋና ርዕሳቸውን ያስተካክላሉ)

2. በቁ.5 መሠረት እግዚአብሔር የተሰሎንቄ ሰዎችን መውደድና መምረጥ እነጳውሎስ ያወቁት በምንድን ነው?

   2.1 ወንጌል በሃይል መምጣቱ በምን ይታወቃል?

   2.2 ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ሲመጣ እንዴት ይታወቃል?

   2.3 ብዙ መረዳት ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ስለሰሚው ነው ወይስ ስለ ሰባኪዎቹ የሚናገረው?

   2.4 ወንጌላችን በቃል ብቻ አይደልም ሲል ስለ ወንጌል ምን ያስተምራል?

3. በቀ.5 ላይ "በእናንተ ዘንድ ስለ እናንተ እንዴት እንደነበርን ታውቃለችሁ" የሚለው ስለየትኛው የእነጳውሎስ ባህርይ ይናገራል? (Hint: በዚሁ ቁጥር እነጳውሎስ ወንጌልን ሲሰብኩ የነበራቸውን ማንነት ያሳያል። ይህም ማንነት ወንጌልን በሃይል፣ በመንፈስ ቅዱስ እና በብዙ መራዳት ውስጥ ሆነው መስበካቸው ነው። ደግሞም እነጳውሎስ ምሳሌ ሆነው ይኖሩ እንደነበርም ያስተምራል።)

4. የተሰሎንቄ ሰዎች ጌታንና እነጳውሎስን የመሰሉት በምንድን ነው?

   4.1 ቃሉን በመንፈስ ቅዱስ ደስታ መቀበል ምን ይመስላል?

   4.2 ቃሉን በብዙ መከራ መቀበል ምን ይመስላል?

5. እነ ጳውሎስ ለተስሎንቄ ሰዎች ምሳሌ እንደነበሩ አሁን ደግሞ እነሱ በመቄዶንያና በአካይያ ላሉተ ሰዎች ሁሉ ምሳሌ ሆነዋል ይላል። ምሳሌ የሆኑት በምነድን ነው?

5.1 የሰበኩት ወንጌልን ሆኖ ሳለ እምነታቸው እንዴት ሊሰማ ቻለ? በቁ.5 ላይ እነጳውሎስ ወንጌልን ሲሰብኩ ከነበራቸው 'ብዙ መረዳት" ጋር ይመሳሰላል?

5.2 እነጳውሎስ ያሉትን ከማመን በተጨማሪ እነሱን መቀበላቸው ፍቅራቸውን እንዴት ያሳያል?

5.3 የተሰሎንቄ ሰዎች ስለነበራቸው ተስፋ ምን ትረዳለህ/ሽ?

መደምደምያ፡- የእነጳውሎስ የምስጋናና የጸሎት ርዕስ የተስሎንቄ ሰዎች እምነት፤ ፍቅርና ተስፋ መሆኑ እነዚህ ሶስት የክርሰትና መለያ ባህርያት ምንያህል አስፈላጊ መሆናቸውን ያስተምራል። ምስጋናህ/ሽና የጸሎት ርዕስህ/ሽ ምንድን ነው? እምነት፤ ፍቅርና ተስፋ በህይወትህ/ሽ ዋነኛ ቦታ አላቸው?

ጥናት ሦስት ወንጌልን በቃልና
በኑሮ መስበክ

የምንባብ ክፍል፡ 1 ተሰ 2፡1-12

የአስተማሪው ማስታወሻ

ቁ.1 ወደ እናንተ መግባታችን የሚለው በ ምዕራፍ 1፡9-10 እንደተገለፀው እነጳውሎስ ወንጌልን ለተሰሎንቄ ሰዎች መስበካቸውና የተሰሎንቄም ሰዎች ይህንን ወንጌል መቀበላቸውን በተጨማሪም እነጳውሎስንም መቀበላቸውን ያሳያል። እዚህ ጋር ጳውሎስ የሚለው የተሰሎንቄ ሰዎች ወንጌሉንና እነጳውሎስን መቀበላቸው በከንቱ እንዳልሆነ ነው። ይህ ማለት ለተስሎንቄ ሰዎች ምንም ጥቅም የሌለው አልነበረም። ከንቱ አለመሆኑን እነጳውሎስ ነግረዋቸው ሳይሆን ራሳቸው በህይወታቸው የመጣውን ለውጥ ስላዩ ያውቃሉ።

ቁ.2 በአምላካችን ደፈርን ማለት ወደገጠማቸው ችግር ሲያዩ ውስጣቸው በፍርሃት ቢሞላም ወደ እግዚአብሔር ሲያዩ ግን ድፍረት አገኙ። በፊሊጵስዩስ የገጠማቸው መከራ የእግዚአብሔርን አምላክነት አለቀየረውም።

ቁ.3 ልመናችን የሚለው በ2ቆሮ 5፡20 እንዳለው ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ የምንለምንበት መለመን ነው። ወንጌል ሲሰበክ በልመና የሚሆንበት ምክንያት ግን ስህተት ስለሆነ ወይም ሰባኪው ንጹህ ስላልሆነ ወይም ለማታለል አይደለም። ጳውሎስ ይህን የሚለው ብዙ ጊዜ ሰዎች የሚለምኑት ወይ ሲሳሳቱ ወይ ንጹህ ካልሆኑ ወይ ደግሞ ሊያታልሉ ሲፈልጉ ስለሆነ ነው።

ቁ.4 እግዚአብሔር ከሆነ የወንጌልን አደራ የሰጠው እሱን እንጂ ሰውን ማስደሰት የለብንም። ከላይ የተጠቀስው መለመን እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ለማስደሰት አይደለም።

ቁ.5 እነጳውሎስ ወንጌልን ሲሰብኩ ሰዎችን ቢለምኑም እንኳ ፈጽመው አያቀላምጡም ነበር። በመጐምጀት የሚለው የተሰሎንቄ ሰዎች ወንጌልን ሲቀበሉ ለእነጳውሎስ ገንዘብ የሚሰጡ ሰዎች እንደሚጨመሩ ያሳያል። እነጳውሎስ እንደዚህ አይነት መጐምጀት አለበራቸውም።

ቁ.6 ልንከብድባችሁ የሚለው እነጳውሎስ የክርስቶስ ሐዋርያት ከመሆናቸው የተነሳ ከተሰሎንቄ ሰዎችም ይሁን ከሌሎች ሊያገኙት ስለሚችሉት የገንዘብ ድጋፍና አክብሮት ነው። ገንዘብንና ሌላን ጥቅም ብቻ ሳይሆን እነጳውሎስ ከተሰሎንቄ ሰዎችም ይሁን ከሌሎች ምንም አይነት የክብር መጐምጀት አልነበራቸውም

ቁ.7 ሞግዚት የሚለው እናት ለማለት ነው። የዋሆች የሚለው እናት ልጆችዋን ስታሳድግ የልጅነታቸውን ጥፋት በቅንነት እንደምታየው እንደዚሁ እነጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች አንዳንዴ ስለእነሱ የተሳሳተ አመለካከት ቢኖራቸውም እነጳውሎስ ግን በቅን ወይም በየዋህነት እንደሚያዩት ያሳያል።

ቁ.8 እነጳውሎስ ለተስሎንቄ ሰዎች የነበራቸው ፍቅር ውንጌልን እስከመስበክ ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውን ወይም ራሳቸውን እስከመስጠት ድረስ ነበር

ቁ.9 እነጳውሎስ ወንጌልን ተከፍሎአቸው ሳይሆን ራሳቸውን ከፍለው ነው የሰበኩት።

ቁ.10 እነጳውሎስ ወንጌልን ላለማስነቀፍ የኖሩትን የቅድስና የጽድቅና ነቀፋ የሌለውን ኑሮአቸውን እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን የተሰሎንቄ ሰዎችም በአይናቸው ስላዩት ምስክሮች ናቸው።

ቁ.11-12 እነጳውሎስ ለተስሎንቄ ሰዎች እንደ እናት ብቻ ሳይሆን እንደ አባትም ነበሩ። አባትነታቸውን ያሳዩት የተሰሎንቄ ሰዎች ወደክብር ለጠራቸው ለእግዚአብሔር በሚገባ እንዲኖሩ በመምከር፣ በማጽናናትና በመለመን ነው። አባት ልጁን እንደሚመክር፣ እንደሚያጽናና እንደሚለምን እንጳውሎስም በአባትነት ፍቅር ይህን ሁሉ አድርገዋልጽና

የጥናቱ ዓላማ:- ወንጌልን ስንሰብክ የምንኖረው ኑሮአችን የምንናገረው የወንጌል ቃል የማያስነቅፍ እንዲሆን ለማነሳሳት

መግቢያ:- ባለፈው ጥናት እነጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የሰበኩት ወንጌል ምን ያህል በሃይል የተሞላና የተሰሎንቄ ሰዎችን ህይወት የለወጠ እንደነበር አይተናል። በዚህ ጥናት ወንጌል ሃይል የሚኖረው ወንጌልን የሚሰብክ ሰው ባህርይ የባላደራን ታማኝነት (1-6) የእናትን ፍቅር (7-8) እና የአባትን ኃላፊነት (9-12) ሲመስል እንደሆነ እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.1 ላይ ከንቱ ማለት ምን ማለት ነው?
   1.1 ራሳችሁ ታውቃላችሁ ማለት ምን ማለት ነው? ራሳቸው የሚያውቁትስ እንዴት ነው?
2. በአምላካችን ደፈርን ማለት ምን ማለት ነው?
   2.1 ድፍረት ያስፈለጋቸው ለምንድን ነው? (በፊሊጵስዩስ ከተቀበሉት መከራ ጋር አሁን ያላቸውን ድፍረት ሲታይ ስለድፍረታቸው ምን መረዳት ይቻላል?)
3. ልመና የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል? መለመን የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?
   3.1 ስሕተት ምንን ያመለክታል?
   3.2 ርኩሰት ምንን ያመለክታል?
   3.3 ተንኮል ምንን ያመለክታል?
4. ሰዎችን ስለወንጌል መለመንና ሰዎችን አለማስደሰት የሚለያዩት እንዴት ነው?
   4.1 እግዚአብሔር ልብን እንደሚመረምር እዚህ ጋር የተጠቀሰው ለምንድን ነው?
5. በመለመንና በማቆለመጥ መሃል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
   5.1 በቁ.5 (እና6) መሰረት እግዚአብሔር ስለእነጳውሎስ የሚመሰክረው ምንድን ነው? (በልባቸው ውስጥ ስውር የሆነ መጐምጀት እንዳልነበረ ነው)
6. ልንከብድባችሁ ሲል የሚያወራው ስለምንድን ነው?
   6.1 ሊከብዱባቸው የሚችሉት ከምን የተነሳ ነው ወይም ይህን መብት የሰጣቸው ምንድን ነው?
7. የዋሆች ማለት ምን ማለት ነው?
   7.1 የእነጳውሎስ የዋህነትና እናት ልጆችዋን ስትንከባከብ የምታሳየውን ባህርይ እንዴት ይመሳሰላል?
8. እነጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የነበራቸው ፍቅር ምን ይመስላል?
9. እነጳውሎስ በተሰሎንቄ ሰዎች ላይ ድካም መሆን ያለፈለጉት ለምንድን ነው?

9.1 ሳይከፈላቸው ወንጌልን መስበካቸው እነጳውሎስ ስለወንጌል ያለቸው አመለካከት ምን መሆኑን ያሳያል?

10. እነጳውሎስ ለኖሩት ቅድስናና ጽድቅ ምስክሩ ማን ነበር?

10.1 እግዚአብሔርም ሰዎችም የሚያዩት ህይወት ማሳየታቸው ለእኛ ምን ያስተምረናል?

11. አባት ለልጆቹ የሚያደርገውና እነጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ያደርጉት የነበሩት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

1. እግዚአብሔር የጠራን ለምንድን ነው?

2. ለእግዚአብሔር እንደሚገባ መመላለስ የሚለውን ምን ማለት ነው?

መደምደምያ:- እኛን ያዳነን ወንጌል ሌሎችን እንዲያድን ከህይወታችን ወንጌልን የሚያስነቅፍ ነገር መወገድ አለበት። ልቤን እግዚአብሔር ያውቃል ብሎ ማሳበብ አያዋጣንም። በእግዚአብሔርም በሰዎችም ዘንድ የሚታይ ህይወት ያስፈልገናል። ይህ ህይወት የባላደራን ታማኝነት (1-6) የእናትን ፍቅር (7-8) እና የአባትን ኃላፊነት (9-12) የሚያሳይ መሆን አለበት።

ጥናት አራት ለወንጌል
ዋጋ መክፈል

የምንባብ ክፍል፡ 1 ተሰ 2፡13-20

የአስተማሪው ማሰታወሻ

**ቁ.13** ስለዚህም የሚለው ከላይ እንጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ወንጌልን ሲሰብኩ በቃለም በኑሮም እንዴት እንደተጉና አሁን የዛ ውጤት ምን እንደሆነ የሚገልጥበትን ሃሳብ የሚያያይዝ ቃል ነው በእውነት እንዳለ የሚለው እነጳውሎስ የሰበኩት ቃል እውነተኛ ማንነቱ ምን እንደሆነ የተሰሎንቄ ሰዎች ማወቃቸውን ያመለክታል። ይህም የሰበኩት የሰውን ቃል ወይም ሃሳብ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

በዚህ ቁጥር የምንማረው ትልቁ ትምህርት የተሰሎንቄ ሰዎች ትልቁ ብርታታቸው ስለ እግዚአብሔር ቃል የነበራቸው አመለካከት መሆኑን ነው። አንደኛ ሰው ቢናገረውም የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር እንደሆነ ማመናቸው። ሁለተኛ የእግዚአብሔር ቃል በሌሎች ህይወት ብቻ ሳይሆን ካመኑበት በእነሱም ህይወት እንደሚሰራ ማስተዋላቸው ትልቁ ብርታታቸውና የሚያገለግሉአቸውን እነጳውሎስን ያስደሰተ ነው።

ቁ.14 ያንን መከራ የሚለው በይሁዳ ያሉ አማኞች ስለወንጌል የተቀበሉትን አይነት መከራ የተሰሎንቄ ሰዎች እየተቀበሉት መሆናቸውን ያሳያል

የምትመስሉ ሆናችሁ የሚለው የተሰሎንቄ አማኞች ጌታንና እንደነጳውሎስ አይነት አገልጋይን ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ቅዱሳንም ህይወት እየተማሩ እነሱን ለመምስል እንደሚጥሩ ያሳያል

ቁ.15 በዚህ ቁጥር በይሁዳ ያሉትን አማኞች ሰላሳደዱ አይሁዳውያን በዝርዝር እናያልን። ጌታ ኢየሱስንና ነቢያትን የገደሉ እነጳውሎስን ያሳደዱ፤ ስለእግዚአብሔር የቀኑ ቢመስሉም እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኙ፤ ለክርስትያኖች ብቻ ሳይሆን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም የማይኖሩ ናቸው ።

ቁ.16 ኃጢያታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ የሚለው የኃጢያታቸውን ጽዋ ይሞሉ ዘንድ ማለት ነው። እግዚአብሔር በ አንድ ጊዜ አይፈርድም፤ ይልቅ ሰዎችን ከኃጢያታቸው እንዲመለሱ ይታገሳቸል፤ ሰው ከኃጢያቱ ካለተመለሰ በየጊዜው የሚሰራው ኃጢያት ጽዋውን ትሞላለች። በእግዚአብሔር አይን የኃጢያት ጽዋው የሞላ ሰው ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ አይችልም። ለዚህም ነው ቁጣው ወደ እነርሱ ፈጽሞ ደርሶአል የሚለው። የ አይሁዳውያንን ታሪክ ስናጠና ከነጳውሎስ ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን የእግዚአብሔር ቁጣ እንዴት እንደደረሰባቸው እናያለን።ፈጽሞ የሚለው በሙላት ማለት ነው። እነሱ ኃጢያታቸውን እንደሞሉ እግዚአብሔር ደግሞ ቁጣውን ሞላባቸው።

ቁ.17 በልብ ያይደለ የሚለው እነጳውሎስ በአካል ከተሰሎንቄ ሰዎች የራቁ ቢሆኑም በልባቸው ግን ሁሌ ስለ እነሱ ስለሚያስቡና ስለሚጸልዩ በልባቸው ለእነሱ ቅርብ መሆናቸውን ያሳያል። መከራ እነጳውሎስን በአካል ከተሰሎንቄ ሰዎች መለየት ቢችልም ከልባቸው ግን ማውጣት መለየት አይችልም።

ቁ.18 ሰይጣን አዘገየን የሚለው በአግዚአብሔር ፈቃድ ሰይጣን ሰዎችንና ሁኔታዎችን ተጠቅሞ የጳውሎስን ጉዞ መግታቱን ያሳያል።

ቁ.19-20 እነጳውሎስ ሲያገለግሎ የጌታን መምጣት እያሰቡ ነው። ጌታ ሲመጣ ደግሞ ለአገልግሎታቸው ሽልማት ይሰጣል። እነጳውሎስ ግን ተስፋ የሚያደርጉት ሽልማታቸው ራሳቸው የተሰሎንቄ ሰዎች እንጂ ሌላ አክሊል አይደለም። ይህ ማለት ጌታ ሽልማት አይሰጣቸውም ማለት ሳይሆን እነሱ ግን ከሚያገኙት ሽልማት በላይ ደስ የሚላቸው በተሰሎንቄ ሰዎች መዳንና ለጌታ ቀን መብቃት ነው። ሰዎች ከቁጣ ድነው ለጌታ መምጣት ሲዘጋጁና ሲድኑ ማየትን ደስ ሊያሰኝ ይገባል።

የጥናቱ ዓላማ:- የምናምነውና የምንሰብከው ወንጌል በእምነታችን ስራ በፍቅራችን ድካም አና በተስፋችን ጽናት የተደገፈ መሆን እንዳለበት ለማሳየት ነው።

መግቢያ:- ባለፈው ሳምንት እነጳውሎስ ያመኑበትን ወንጌል ለተሰሎንቄ ሰዎች በቃል ብቻ ሳይሆን በኑሮአቸውም እንዴት እንደሰበኩ አይተናል። ዛሬ ደግሞ የተሰሎንቄ ሰዎች ራሳቸው የተሰበካለውን ወንጌልን እንዴት እንዳመኑና ለእምነታቸውን የከፈሉት ዋጋ እንዴት እንደነበር እንዲሁም እነጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ስለነበራቸው ፍቅርና ተስፋ እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.13 መሰረት የእነጳውሎስ የምስጋና ርዕስ ምንድን ነው?

    1.1 የተሰሎንቄ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ቃል ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

    1.2 የእግዚአብሔር ቃል የሚሰራው ለማን ነው? ይሰራልስ ሲል ምን ማለት ነው?

    1.3 ሰዎች የሚናገሩት የእግዚአብሔር ቃል ይሁን አይሁን የሚታወቀው እንዴት ነው? (Hint: ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲወጣና በሰዎች ህይወት ሲሰራ ነው)

2. በምዕራፍ አንድ የተሰሎንቄ ሰዎች ጌታንና እነጳውሎስን እንደመሰሉ አሁን ደግሞ ሌሎች ቅዱሳንን መምሰላቸው ስለተሰሎንቄ አማኞች ምን ይናገራል?

    2.1 በይሁዳ ያሉትን አማኞችን የመሰሉት እንዴት ነው?

    2.2 የአማኞችን ሁሉ ስለወንጌል የሚቀበሉትን መከራ አንድ የሚያደርገው ምንድን ነው? (hint: መከራው ከተለያዩ ሰዎች ቢሆንም ስለ አንዱ ወንጌል መሆኑ አንድ ያደርገዋል፤ የአማኝ መከራ ከባህርይ ችግር ሳይሆን ከወንጌል የተነሳ ነው)

3. የአይሁዳውያን ኃጢያት ምን ነበር?

    3.1 ኃጢያታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ የሚለው ምን ማለት ነው?

    3.2 በቁ.16 እግዚአብሔር የተቆጣው ማንን ነው? ቁጣውስ ምድን ነው? ፈጽሞ ደርሶአል ሲል ምን ማለቱ ነው?

4. በቁ17 እና18 እነጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ስለነበራቸው ፍቅር ምን እንማራለን?

    4.1 በአካል እንጂ በልብ አለመራራቅ ማለት ምን ማለት ነው?

    4.2 ናፍቆትና ለማየት እጅግ ሞከርን የሚሉት ስለነጳውሎስ ፍቅር ምን ያስረዳል?

5. በቁ19 እና 20 እነጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች ደስታችን ናችሁ ሲሉአቸው ምን ማለታው ነው? ሰው እንደት ነው ደስታ የሚሆነው?

    5.1 ተስፋችን ናችሁ ሲሉስ ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር የሰው ተስፋ ከመሆኑ ጋር ሲስተያይ ተስፋችን ናችሁ ማለታቸውን እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?

    5.2 አክሊላችን ናችሁ ማለት ምን ማለት ነው?

6. ከቁ.13-16 የተሰሎንቄ ሰዎችን የእምነታውን ስራ፤ ከቁ.17-18 የእነጳውሎስን የፍቅር ድካም፤ ከቁ.19-20 የተስፋቸውን ጽናት በማየት በአሁኑ ዘመን ላለን አማኞች ምን ትምህርት ይቀርልናል። መደምደምያ፡- ያዳነንን ወንጌል እንደሚሰራ ካመንን ስለዘህ ወንጌል የመጣውን መከራ ልንቀበልና ዋጋ ልንከፍል ይገባናል። መከራ መቀበላችን በእርግጥ ወንጌል እንደሚሰራ ማመናችንን ያሳያል። ሰው ለማይሰራ ነገር መከራ አይቀበልም። ከእምነታችን ስራ በተጨማሪ፣ ለቅዱሳንና ለማያምኑ ያለንን ፍቅር በምንደክምላቸው ድካም መግለጥ አለብን። ዘሬ በመከራና በድካም ብንኖርም ጌታ ሲመጣ የሚሰጠንን ብድራት ተስፋ ልናደርግ ይገባናል።

ጥናት አምስት
በተስፋ መጽናት

የምንባብ ክፍል፡ 1 ተሰ 3፡1-13

የአስተማሪው ማስታወሻ

**ቁ.1** ስለዚህ የሚለው ምዕራፍ ሦስትን ከምዕራፍ 2፡17-20 ጋር የሚያይዝ ነው። እነጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች ለማየት ብዙ ቢናፍቁና ቢሞክሩም በተለያየ ምክንያት አልቻሉም። በዚህ ክፍል እነጳውሎስ መታገሥ ያልቻሉት የተሰሎንቄ ሰዎችን ናፍቆት ነው ። በሐዋርያት ስራ 17 እንደምናየው ጳውሎስና ሲላስ በተሰሎንቄ ስደት ሲመጣባቸው ወደ ቤርያ ከዛም ጳውሎስ ወደ አቴና እንደሄደ እናነባለን። ሲላስና ጢሞቴዎስም በአቴና ከጳውሎስ ጋር አብረው ነበሩ። በተሰሎንቄ የነበረው ስደት በተለይ ጳውሎስና ሲላስ ላይ ያተኮረ ስለነበር ጢሞቴዎስን ሊልኩት ወደዱ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ካለው ፍቅርና ጢሞቴዎስም ጳውሎስን በብዙ አይነት መልኩ ይረዳው ስለነበር ጢሞቴዎስን መላክ ከባድ ነበር። ቢሆንም ለተሰሎንቄ ሰዎች ያለው ፍቅርና የ እነሱ ህይወት ጥያቄ ከራሱ ስለበለጠበት ጢሞቴዎስን ላከው።

**ቁ.2** ጳውሎስ ስለጢሞቴዎስ የሚያየው 1) እንደወንድም 2) እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ 3) አብሮ የሚሰራ ሰራተኛ። ጳውሎስ ከጢሞቴዎስ ራሱን በምንም አላስበለጠም፤ ይልቁን እንደ እኩያው ነው ያየው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወደተሰሎንቄ የላከበት ምክንያት 1) እንዲያጸናቸው 2) በእምነታቸው እንዲመከራቸው ነው። የዳነ ሰው ሁሉ በዳነበት ወንጌል ላይ ያለማቋረጥ መቆም እንዳለበት ያሳያል። የሚመክራቸው በእምነታቸው እንዴት መጽናት እንዳለባቸው በማስረዳትና በማበረታታት እንዲሁም አጥብቆ በማስጠንቀቅ ነው።

**ቁ3.** በዚህ መከራ የሚለው እነጳውሎስም የተሰሎንቄ ሰዎችም ራሳቸው ስለሚቀበሉት ስደት ነው። በእምነታቸው መጽናት ያለባቸው መከራ እንዳያናውጣቸው ነው። ይህ መናወጥ የስሜት የሃሳብ የውሳኔ መናወጥ ነው።መከራው ሊያናውጣቸው የማይገባበት እነሱ ራሳቸው የሚያቁት ነገር ስላለ ነው። ይህ የሚያውቁት ነገር እነሱና እነጳውሎስ በወንጌል ለማመን በእርሱም ለመዳን እንዲሁም ስለ እርሱ መከራ ሊቀበሉ እንደተመረጡ ነው። ፊልጵስዩስ 1፡28-30 “በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ. . . ይህም ከእግዚአብሔር ነው፤ ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በ እርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም . . .” በእግዚአብሔር አጀንዳ ውስጥ ያለከሆነ መከራው ሲመጣ መናወጥ የለባቸው፤ እግዚአብሔር የማያውቀው እነሱም ያለተዘጋጁበት መከራ አይመጣም።

**ቁ.4** እንዲሁም ሆነ የሚለው እነጳውሎስ እንደነገሩአቸው እንደሆነና ድንገተኛ እንዳለሆነ ያሳያል።መከራ በአማኝ ህይወት መጠበቅ አለበት፡ ሲጠፋ እንጂ ሲመጣ መደነቅ የለብንም።ከምዕራፍ 1 ጀምሮ ታውቃላችሁ የሚላቸው እንዳይታለሉ ነው፤ የምንታለለው ሳናውቅ ስንቀር ነው፤ እነጳውሎስም ሆኑ የተሰሎንቄ ሰዎች እግዚአብሔር ያለተናገራቸውና የማያውቁት ነገር አለደረሰባቸውም፤ ጌታ ኢየሱስም ሊቀበለው ስለነበረው መከራ ያውቅ ነበር፤ ስለዚህ ፈተናውን አለወደቀም፤ ማወቅ መዘጋጀት ያስችላል፤ ጌታ ኢየሱስ በጌተሰማኔ ተዘጋጅቶ ነበር፤ እነጳውሎሰ የተሰሎንቄን ሰዎች አስቀድመው በመንገር ያዘጋጁአቸው ነበር፤ እነጳውሎስ ከመዘጋጀታቸው የተነሳ በመከራ ውስጥ እንኳ ሆነው እነሱ ሌሎችን ያጽናኑ፤ ለሌሎች ይጸልዩ ነበር።

**ቁ. 5** ፈታኝ የሚለው ሰይጣን ምን ያህል በመከራ ውስጥ ያለን ሰው እምነቱን ለማስጣል የሚያደርገው ጥረት ነው፤ ኢዮብንም እንደዚህ ፈትኖታል።ሰይጣን ማታለል ነው ስራው፤ የሚመጣብንን መከራ ሰይጣን አመጣው ባንልም እሱ ግን መከራውን ተጠቅሞ ይፈትናል፤ ፈተናው ለማታለል ነው፤ እሱ አታላይ ነው። ጢሞትዮስ እምነታቸውን ሊያበረታታ የመጣው ሰይጣን እምነታቸውን ሊወስድ ስለሚፈልግ ነው። ድካማችን ከንቱ ሆኖአል ብዬ የሚለው እነጳውሎስ መከራ እየተቀበሉ በትጋት ወንጌል ከሰበኩላቸውና ወንጌሉን ካመኑ በኋላ እምነታቸውን ቢጥሉ ድካማቸው ያለፍሬ እንደሚሆን ያሳያል፤ ስለዘህ ጳውሎስ እንዴ ድነዋል ብሎ አላቆመም፤ አገልግሎቱ ቀጣይነት ነበረው።

**ቁ.6-8** ጢሞቴዎስ ስለተሰሎንቄ ሰዎች በ እምነታቸው እና ለነጳውለስ ስላላቸው ፍቅር ዜና ይዞ ወደነጳውሎስ ተመለሰ፤ ይህ ዜና ለነጳውሎስ ትልቅ ደስታ ነበር፤ በሚቀበሉት መከራ እንኳ መጽናናት ሆናቸው። እናንተ በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ አሁን በሕይወት እንኖራለንና የሚለው የተሰሎንቄ ሰዎች እምነታቸውን መጣል ለእነጳውሎስ

ሞት በእምነት መጽናት ግን ሕይወት አድርገው እንደሚያዩት ያሳያል። በ 2፡19-20 ላይ የተሰሎንቄ ሰዎች ተስፋቸው፤ ደስታቸውና አክሊላቸው እንደሆኑ፤ አሁን ደግሞ የነሱ በጌታ መኖር ለእነጳውሎስ በሕይወት የመኖር ያህል ነው የሚሰማቸው፤ ይህ ለነሱ ያላቸውን ፍቅር ያሳል ።

ቁ.**9-11** በእምነታችሁ የጐደለውን ልንሞላበት የሚለው እንጳውሎስ በአካል በተሰሎንቄ ሰዎች ዘንድ ሆነው ሊያስተምሩአቸውና ሊያደርጉት ስለሚያቅዱት ነው የሚያወራው። ነገር ግን ከእምነታቸው ምን እንደጐደለ ግልፅ አይደለም። ዋናው ነጥብ የጐደለን ነገር ዝም ብሎ ማየት አለመፈለጋቸው ነው። በምዕራፍ አንድ እንዳየነው አሁንም እነጳውሎስ በጸሎትም በምስጋናም ይተጉ ነበር። በተሰሎንቄ ሰዎች እምነት የጐደለ ነገር ስለነበር ከመጠን ይልቅ ይጸልዩ ነበር።

ቁ.**12-13** ጳውሎስ በምዕራፍ አንድና ሁለት መጨረሻ ላይ እንዳረገው አሁንም ስለ ኢየሱስ ዳግም መምጣት ይጠቅሳል። ይህ የእነጳውሎስን የተስፋ ጽናት ያሳል። የጌታን መምጣት የሚጠቅሰው የተሰሎንቄም ሰዎች በዚህ ተሰፋ እንዲጸኑ ነው። ከ እምነትና ተስፋ በተጨማሪ በፍቅርም እንዲጸኑ ይጸልይላቸዋል። ይህ ፍቅር እነጳውሎስ እነሱን እንደሚወዱ አነሱም አርስ በርሳቸውና ሌሎችን እንዲወዱ ነው።

<u>የጥናቱ ዓላማ:-</u> በወንጌል ተለውጠን ያገኘነውን እምነት፤ ፍቅርና ተስፋ አጥብቀን መያዝ እንዳለብን ለማሳየት።

<u>መግቢያ:-</u> በምዕራፍ አንድ የተሰሎንቄ ሰዎች የሰሙት ወንጌል ወደፊት ስላላቸው ተስፋ እንዳስረዳቸውና በዚህም ተስፋ ላይ እምነታቸውን እንደጣሉ፤ ከተስፋውም የተነሳ እርስ በርሳቸው ይዋደዱ እንደነበር አይተናል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ እነጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች በእምነታቸው በፍቅራቸውና በተስፋቸው እንዲጸኑ ስላደረጉት ነገር እናያለን። እነዚህ አንዴ ጀምረን የምንተዋቸው ሳይሆኑ እስከ መጨረሻ ድረስ ልንይዛቸው የሚገቡ መሠረታዊ የከርስተና ምሶሶዎች እንደሆኑ እናያልን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ስለዚህ የሚለው ስለምንድን ነው የሚያወራው?

    1.1 እነጳውሎስ መታገሥ ያልቻሉት ምንድን ነው?

2. ጢሞቴዎስ የተላከበት አላማ ምን ምን ነው?

3. ጳውሎስ ስለጢሞቴዎስ የሚላቸውን ሦስት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

4. በቁ.3 ለዚህ እንደተመረጥን የሚለው ስለማን ነው?

    4.1 ስለምን አይነት መመረጥ ነው የሚያወራው?

    4.2 ታውቃላችሁ የሚላቸው ለምንድን ነው?

5. እነጳውሎስ ሊመጣ ስላለው መከራ አስቀድመው መናገራቸው ጥቅሙ ምንድ ነበር?

6. ቁ.5 ፈታኝ የሚለው ማንን ነው?

    6.1 ፈታናው ምንድን ነው?

    6.2 በዚህ ክፍል መሰረት የፈተናና መከራ ልዩነት ምንድን ነው?

7. በቁ.6 ጢሞቴዎስ ለእነጳውሎስ ስለተሰሎንቄ ሰዎች ያመጣው የምስራች ምነድን ነው?

7.1 በቁ.7 የምስራቹ እነጳውሎስ ውስጥ የፈጠረው ምንድን ነው?

8. በቁ.8 በሕይወት እንኖራለን የሚለውን አብራራ/ሪ

9. እነጳውሎስ ከመጠን ይልቅ ሌትና ቀን የሚጸልዩት ስለምንድን ነው?

9.1 ከመጠን ይልቅ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? (Hint: እምነታቸው ውስጥ የጐደለ ነገር ስለነበር ነው)

10. የተሰሎንቄ ሰዎች ምን አይነት ፍቅር እንዲኖሩ ነው እነጳውሎስ የሚጸልዩት?

11. ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ የሚለው እነጳውሎስ በጌታ መምጣት ላይ ስላላቸው ተስፋ ምን ይናገራል?

12.

11.1 ስለጌታ መምጣት መጥቀሱ ለተሰሎንቄ ሰዎች ምን ይጠቅማል?

<u>መደምደምያ:-</u> እነጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች በእምነታቸው በፍቅራቸውና በተስፋቸው እንዲጸኑ በጸሎት፤ አገልጋዮችን በመላክና በደብዳቤ፤ በነገር ሁሉ ይተጉ ከነበር እኛስ እነዚህን ነገሮች በእኛ ውስጥ ለመጠበቅ ምን ያህል እንተጋልን? ለመትጋት እንችል ዘንድ ድግሞ በ እነዚህ ነገሮች መጽናት እነድዳለብን ምን ያህል አስተውለናል?

ጥናት ስድስት
ቅዱስ ፍቅር

የምንባብ ክፍል፡- 1 ተሰ 4፡1-12

የአስተማሪው ማስታወሻ

**1.** እንግዲህ በቀረውስ የሚለው ዋና መልዕክቱን ጨርሶ ወደ መደምደምያው ሃሳብ እየሄደ እንደሆነ ያሳያል። ከምዕራፍ አንድ እስከ ሦስት እንደተገለጸው የመልዕክቱ ዋና ሃሳብ የተሰሎንቄ ሰዎች በ እምነት በፍቅርና በተስፋ ጸንተው እንዲኖሩ ለማሳሰብ ነው።

ከእኛ ዘንድ እንደተቀበላችሁት ማለት ከእኛ እንደተማራችሁት ማለት ሲሆን በተጨማሪም የተማሩት ነገር ባደራ መልክ ለእነሱ እንደተሰጣቸውና እነሱም እንደተቀበሉት ያሳያል

ይህ የተቀበሉት ትምህርት 1) እንዴት መኖር እንዳለባቸውና 2) እንዴት እግዚአብሔርን ማስደሰት እንዳለባቸው ነው

የተሰሎንቄ ሰዎች የእውቀት ችግር የለባቸው ህይወታቸውን እንዴት መኖር እንዳለባቸውና እግዚአብሔርን እንዴት ማስደስት እንዳለባቸው ያውቃሉ፤ ማወቅም ብቻ ሳይሆን እንደተማሩት እየኖሩ ነው፤ ከፊት ይልቅ ትበዙ ዘንድ ማለት በቁጥር መብዛት ሳይሆን ልክ እንደተማሩት መኖር ይበዛላቸው ዘንድ ነው፤ በምዕራፍ ሦስት ላይ በ እምነታቸው በፍቅራቸውና በተስፋ መመላለሳቸውን እንዲቀጥሉ እንደመከራቸው አሁንም የሚመከራቸው ያላቸውን ነገር እንዲያበዙት ነው

ያላቸውን ነገር እንዲያበዙ ጳውሎስ ትዕዛዝ ሳይሆን የሚሰጣቸው ልመናና ምክር ነው፤ ትዕዛዝ ለማይታዘዝ ሰው ነው፤ እነሱ ግን እየታዘዙ ያሉ ሰዎች ስለሆኑ መለመንና ማበራታታት ብቻ ይበቃቸዋል

**2.** በዚህ ቁጥር የምናየው የተሰሎንቄ ሰዎች ትዕዛዝን ከዚህ በፊት ተቀብለው እንደነበር ነው፤ የታዘዙት ትዕዛዝ ምን እንደሆነ ስለሚያውቁ ጳውሎስ ሌላ ትዕዛዝ አለሰጣቸውም፤ እነጳውሎሰ ትዕዛዝ መስጠት የቻሉት ጌታ ኢየሱስ ከሰጣቸው ሃላፊነት የተነሳ ነው፤ ይህ የሚነግራቸው የሰጣቸውን ትዕዛዝ ከጌታ እንደሆነ አድርገው እንዲቀበሉት ለማበረታታት ነው

**3.** የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚለው በቁጥር አንድ ላይ ከእኛ ተቀበላችሁ ስላላቸው ሁለት ጉዳዮች ነው፤ ህይወታቸውን እንዴት መኖር እና እግዚአብሔርን እንዴት ማሰደሰት እንዳለባቸው ለማወቅ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው ብለው ሲጠይቁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ግራ የማያጋባ አጠያያቂ ያልሆነ እንደሆነ አረጋግጦ ይነግራቸዋል፤ ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በህይወቱ ለማወቅ ቢፈልግ መልሱ፡ መቀደስ ነው፤ ቅድስና የሌለበት ነገር ሁሉ የእግዚአብሔረ ፈቃድ አይደለም፤ የቅድስናን ትርጉም ከቁጥር 4 እስከ ቁጥር 8 ድረስ ይሰጣል

**4-5.** ቅድስና 1) ከዝሙት መራቅ ነው. ዝሙት በትዳር ካተሳሰሩት ሰው ጋር ወሲብ መፈጸም ነው፤ በትዳር መተሳሰር ማለት ሁለት ሰዎች በሰዎችና በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን ገብተው የሚኖሩት የዕድሜ ልክ ኑሮ ነው. እንደዚህ ሳይተሳሰሩ ወሲብ መፈጸም ዝሙት ነው፤ ይህ ደግሞ ቅድስናን ማጣት ነው፤ ቅድስና ማጣት ደግሞ ግልጥ የሆነውን የ እግዚአብሔርን ፈቃድ መተላለፍ ነው 2) ከፍትወት ምኞት መራቅ ነው፤ ጌታ ኢየሱስ እንዳስተማረው ዝሙት አንድ ሰው ወሲብን በ አካል ሲፈጽም ብቻ እንዳልሆነ ነገር ግን ሰው በልቡ ሲመኝ ያኔ ወሲብን እንደፈጸመና ዝሙትን እንዳደረገ ነው፤ 3) የራስን ዕቃ(የሰውነት ክፍሎቻችንን-ልብ፤ አዕምሮ፤ አንደበት፤ ብልቶቻችንን ሁሉ) በቅድስናና በአክብሮት መያዝ ነው፤ የሰውነትን ክፍል በቅድስናና በአክብሮት መያዝ ማለት ለተፈጠሩበት አላማና ለተፈቀደለት ጉዳይ ብቻ መጠቀም ነው፤

**6.** ጌታ የሚበቀል ነው የሚለው ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ቅድስናውን የሚያበላሽን ሰው እንደሚቀጣ ነው፤ እነጳውሎስ አስቀድመው የነገሩአቸው እግዚአብሔር በበቀሉ እንዳይገለጥባቸው ነው እንደመሰከርንላችሁ የሚለው ግልጥ አድርገውና በማስረጃ አስደግፈው እግዚአብሔር የማይቀደስን ሰው እንዴት እንደሚበቀል መናገራቸውን ነው

ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ ወንድሙንም አያታልል ሲል ክርስትያን ወንድምን ወይም እህትን ለዝሙት የሚያታልልን ሰው ነው፤

**7.** እግዚአብሔር የጠራን ወይም የዳንበት ምክንያት እንድንቀደስ እንጂ ድነናል ብለን ልቅ ሆነን እንድንኖር አይደለም፤ ይህ በቁጥር 3 ላይ መቀደሳችሁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብሎ ያለውን እስረግጦ ይናገራል፤

**8.** የሚጥል የሚለው ስለቅድስና የተሰጠውን ትዕዛዝ አለመቀበልን ነው፤ ትዕዛዙ በሰው በኩል ይሰጥ እንጂ ከ እግዚአብሔር ስለሆነ የተሰጠው ትዕዛዙን የማይቀበል ሰው እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም ያልተቀበለው

**9.** በእግዚአብሔር ተምራችኃል ማለት በህይወታቸው እግዚአብሔር ስላስተማራቸው ትምህረት ነው፤ እነጳውሎስ በቃል ቢያስተምሩአቸውም እግዚአብሔር ብቻ ነው የሰሙትን በህይወታቸው እንዴት መተርጎም እንዳለበት እያሳየ፤ አቅም እየሰጠ የሚያስተምረው፤ እርሱ የሚሰጠው ትምህርት አድርጉ እያለ ማለት ሳይሆን እንዴት ማደረግ እንዳለብን እያሳየ የምናደርግበትን አቅም መስጠት ነው

**10-12** ከፊት ይልቅ ልትበዙ ሲል ቁጥራቸውን ሳይሆን መልካም ነገራቸውን በጎ ልምምዳቸውን የፍቅራቸውን መብዛት ነው፤ ይህ በ እግዚአብሔር ተምረው ያገኙት ፍቅር አሁን እንዲበዛ የተፈለገው በሦስት ጉዳዮች ላይ ነው፡
1) በጸጥታ ልትኖሩ፤ ያለማጉረምረም፤ ሳይረበሹ፤ ራሳቸው ሳይታወኩ ሌሎችንም ሳያውኩ ስለመኖር ነው የሚያወራው
2) የራሳችሁን ጉዳይ ልትጠነቀቁ፤ ይህ ማለት ስለሌሎች ግድ አይበላችሁ ማለት ሳይሆን ስራ የፈታ ሰው የሚሰራው ሲያጣ ሌሎችን ለመርዳት ሳይሆን እንዲሁ ስለሌሎች ጉድለት እያወራ በሌሎች ድካም ላይ ጊዜውን ሲያጠፉ ነው፤ ሰው በራሱ ድካም ላይ አይኑን ማድረግ አለበት፤ 3) በእጃችሁ ልትሰሩ ሲል ጌታ በቶሎ ይመጣል ብለው ስራቸውን አቁመው የሚኖሩ ሰዎችን ይመለከታል፤ እነዚህ ሰዎች እየኖሩ ያሉት ከሌሎች በሚያገኙት ነው፤ ስራ መስራት እየቻሉ ባለመስራት ሌሎች ላይ ሸክም መሆን ለነዛ ሰዎች ፍቅር አለመኖር ነው፤ ለሰዎች ፍቅር ሲኖረን ሸክም አንሆንባቸውም

በእነዘህ ሦስት ጉዳዮች ፍቅራቸው ሲበዛ ሁለት ነገር ይሆናል፤ 1) በውጭ ባሉት ዘንድ (በማያምኑት) በአግባብ ይኖራሉ፤ የጌታን ስም አያስነቅፉም 2) አንዳችም እንዳያስፈልጋችሁ፤ ምንም አይጎድላቸውም፤ ሌሎች ላይ ሸክም አይሆኑም

<u>የጥናቱ ዓላማ፡-</u> ለወንድሞችና ለእህቶች ያለን ፍቅር ከእነሱ ጋር በቅድስና እንድንኖር፤ በዝሙት እንዳንበድላቸው፤ እንዳናውካቸው፤ በችግራቸው እንዳንጠቄቆምባቸውና ሸክም እንዳንሆንባቸው ለማበረታታትና ለማስጠንቀቅ ነው

<u>መግቢያ፡-</u> በምዕራፍ ሦስት ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች በእምነታቸው በፍቅራቸውና በተስፋቸው ጸንተው እንዲኖሩ አስተምሮአቸዋል፤ ስለፍቅር ሲነግራቸው በቁ.12-13 ላይ ለእርስ በ እርሳቸው ያላቸው ፍቅር በቅድስናና ነቀፋ በሌለበት ፍቅር እንዲኖሩ እንደሚያረጋቸው ተናግሮአል፤ በዚህ ክፍል ፍቅር እንዴት በቅድስናን መኖር እንደሚያስችል ያሳይል፤ ከቁ.1-8 ፈቅር በሌላው ላይ ዝሙትን እንዳንፈጽም ያደርጋል፤ ፍቅር ሲኖር ሰው ዝሙት አይፈጽም፤ ከቁ.9-12 ፈቅር በጸጥታ ያኖራል፤ በራሳችን ጉዳይ (ድካም ላይ) እንድናተኩርና ለሌሎች ሸክም እንዳንሆን ያደርጋል

<u>የመወያያ ጥያቄዎች፡</u>

1. ከእኛ ዘንድ እንደተቀበላችሁት ማለት ምን ማለት ነው

   1.1. ይህ የተቀበሉት ትምህርት ምን ምን ነው?

   1.2. ከፊት ይልቅ ትበዙ ዘንድ ማለት ምን ማለት ነው?

   1.3. ጳውሎስ እንለምናችለን እንመክራችለን የሚለው ለምንድን ነው?

2. እነጳውሎሰ ሰዎች ሆነው ሳለ ለሌሎች ትዕዛዝ መስጠት የቻሉት ከምን የተነሳ ነው?

3. በዚህ ቁጥር መሰረት ለቅዱሳን ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው?

4. በ ቁጥር 4-5 ቅድስና የተገለጠባቸው ሦስት መንገዶች ምን ምን ናቸው?

   4.1. ዝሙት ምንድን ነው?

   4.2. የፍትወት ምኞት ምንድን ነው?

   4.3. የራስን ዕቃ በቅድስናና በአክብሮት መያዝ ማለት ምን ማለት ነው?

5. በቁጥር 6 መሠረት ጌታ የሚበቀል ማንን ነው? ለምንድን ነው? መበቀል ሲልስ ምን ማለት ነው?

   5.1. እንደመሰከርንላችሁ የሚለው ምን ማለት ነው?

   5.2. ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ ወንድሙንም አያታልል ሲል ስለምንድን ነው?

6. በቁጥር 7 መሠረት እግዚአብሔር የጠራን ወይም የዳንበት ምክንያት ለምንድን ነው?

7. በቁጥር 8 የሚጥል የሚለው ምንን ስለመጣል ነው?

8. በቁጥር 9 በእግዚአብሔር ተምራችኃል ማለት ምን ማለት ነው?

9. በቁጥር 10-12 ከፊት ይልቅ ልትበዙ ሲል ስለምን አይነት መብዛት ነው የሚናገረው? (Hint: ስለ ቁጥር ሳይሆን ስለበጎ ነገራቸው/ስለፈቅራቸው መብዛት ነው)

   9.1. ፍቅራቸው የሚገለጥበት ሦስት መንገዶች ምን ምን ናቸው?

   9.2. በጸጥታ ልትኖሩ ማለት ምን ማለት ነው?

   9.3. የራሳችሁን ጉዳይ ልትጠነቀቁ ማለት ምን ማለት ነው?

   9.4. በእጃችሁ ልትሰሩ ማለት ምን ማለት ነው?

   9.5. ፍቅራቸውን ከላይ በተጠቀሱት ሦስት መንገዶች መግለጣቸው የሚጠቅማቸው ለምንድን ነው?

   9.6. በውጭ ባሉት ዘንድ (በማያምኑት) በአግባብ መኖር ማለት ምን ማለት ነው?

   9.7. አንዳችም እንዳያስፈልጋችሁ ማለት ምን ማለት ነው?

መደምደምያ:- የተሰሎንቄ ሰዎች ለእርስ በርሳቸውም በሌላ ቦታ ላሉ ቅዱሳንም ያላቸውን ፍቅር ቅድስና ያለበትን ነገር በማድረግ እንዲያሳዩና ለማያምኑት ጥሩ ምሳሌ መሆን እንዲችሉ ጳውሎስ አበረታትቶአቸዋል፤ እኛም ፍቅራችንን በስራ ልንተረጉመውና ለማያምኑት ልናሳየው ይገባል፤ ለተሰሎንቄ ሰዎች የእግዚአብሔር ፍቃድ ቅድስና እንደነበር ለኛም የእሱ ፈቃድ ያው ነው፤ ስለዚህ ፍቅራችንን በቅድስናን ወደሚገለጥበት ደረጃ ልናደርሰው ይገባናል።

ጥናት ሰባት አፅናኝ
ተስፋ

የምንባብ ክፍል፡ 1 ተሰ 4፡13-18

የአስተማሪው ማስታወሻ

**13.** ተስፋ እንደሌላቸው ሲል በጌታ ያልሆኑ ሰዎች ከሞት በኋላ ምንም አይነት ተስፋ እንደሌላቸው ያሳያል፤ በዚህም ዘመን እያንዳንዱን ሃይማኖት ብናይ፣ ከሞት በኋላ ስላለው ጊዜ ተስፋ የሚሰጥ ሃይማኖት የለም፤ የተወሰኑ ሃይማኖቶች የሚያወሩት ተስፋ ደግሞ፤ በመልካም ስራ ላይ የተመሰረተ ነው፤ በጌታ ያለው ተስፋ ግን እርሱ በሰራው ስራ እንጂ በእኛ ስራ አይደልም፤

እንቀላፍተው ስላሉቱ ሲል በጌታ አምነው ስለሞቱ ሰዎች ነው፤ በጌታ ያመኑ ሰዎችን ከሌሎች የሚለየው ከሞት በኋላ ያለው ተስፋ እንጂ አለመሞት አይደለም፤ ሞት ክርስትያንንም ያገኛል፤ ነገር ግን የማያምኑትን ወደ ዘላለም ጥፋት ሲያሸጋግር የሚያምኑትን ግን ወደ ዘላለም ዕረፍት ያሸጋግራል፤ አሁን የሞቱትን ብቻ ግን ሳይሆን በህይወት ስለምንኖር ሰዎችም ነው የሚናገረው፤ ጌታ ቀድሞ ካለመጣ በስተቀር ሞት ወደ እኛም ሊመጣ ይችላል፤

እንዳታዝኑ ሲል በጌታ አምነው ሰለሞቱት ወገኖቻችንም ቢሆንን እኛም አንድ ቀን እንሞት ይሆናል ብለን ልናዝን እንችላለን፤ ሞት ሃዘንን ያመጣል፤ የአማኝ ሃዘን ግን ተስፋ እንደሌላቸው ሰዎች ሃዘን መሆን የለበትም፤ ማዘናችን ሳይሆን ተስፋ እንደሌላቸው ሰዎች ሆነን ማዘናችንን የእግዚአብሔር ቃል ይቃወመናል፤

ታውቁ ዘንድ የሚለው ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት አማኞች ሁሉ ማወቅ ያለባቸው ነገር እንዳለ ያሳያል፤ እንዳናዝን የሚረዳን ይህ እውቀት ነው፤ እንደሌሎችም የምናዝነው ስለማናውቅ ወይም ስላላስተዋልነው ነው፤

**14.** ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሳ ካመንን የሚለው የክርስትና መሰረቱ የጌታችን የ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ እንደሆነነ ነው፤ ይህንን ከልቡ ያላመነ ሰው ሰለ ጌታ ዳግመኛ መምጣት ወይም ስለ አማኞች ትንሳኤ ቢነገረው ለማመን ይቸገራል፤ ስለዚህ ሁላችን የጌታችንን ሞትና ትንሳኤ ከልባችን ልናምነው ይገባል፤ በዚህ ላይ ጥርጥር ካለን ቃሉን ማንበብና በህይወታችን ህያውነቱን ልናይ እንችላለን፤ ጌታ ሞቶ ያልተናሳ ከሆነ በህይወታችን የምናየውን ለውጥ አናይም ነበር፤ የሌሎችንም ህየውት ማየት እንችላልን፤ ቃሉንም ስናነብ በውስጣችን ያለውን ሃይሉን አይተን ትንሳኤውን ማወቅ እንችላለን፤ የአይን ምስክሮች የሆኑ ተከታዮቹ ስለነገሩንም እናምናለን፡ ተነስቶ ባያዩት ኖሮ ስለትንሳኤው እየተናገሩ ራሳቸውን ለሰይፍ አሳልፈው አይሰጡም ነበር፤

በኢየሱስ ያንቀላፉቱን የሚለው ኢየሱስን አምነው በስጋ ከዚህ አለም በሞት የተለዩትን ማለቱ ነው

ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል ሲል ጌታ ኢየሱስ ዳግመኛ ሲመጣ አሁን ሞተው ያሉ አመኞችንም ይዞ እንደሚመጣ ያሳያል፤ ይህ ዳግመኛ ምጣት የጌታ ብቻ ሳይሆን የአማኞችም ነው፤

**15.** በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህንን ነው የሚለው የዳግመኛ ምጣት እውነት የሰው ቃል ሳይሆን ከ እግዚአብሔር ከራሱ የወጣ እንደሆነ ነው፤ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ሁሉ ደግሞ በርሱ ጊዜ ይፈጸማል፤ እምነታችንን የጣልነው በ እግዚአብሔር ላይ እንጂ በሰው ላይ አይደልም፤ ስለጌታ ኢየሱስ የመጀመርያ መምጣት ስናስብ ትንቢቱ የተነገርወ በገነት ጀምሮ ነው ግን የተፈጸው ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው፤ ጊዜ ቢወስድም የ እግዚአብሔር ቃል ይፈጸማል፤

እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር የሚለው በዚህ ምድር በህይወት ስላለን አማኞች ነው፤ በተለምዶ ምንም እንኳ ጌታ መጥቶ እንደሚወስደን ወይም እንደምንሞት ብንናገርም ከዘህ ክፍል የምንማረው ልንናገር የሚገባን ስለጌታመምጣት እንጂ ስለሞት አይደለም፤ ጌታ ካልመጣ እኛ በሞት ወደሱ እንሄዳለን፤ ነገር ግን ሁል ጊዜ ቶሎ እንደሚመጣ እያሰብን ልንኖር እንደሚገባን ያሳያል፤ ሞትን ልናዘገየው እንችል ይሆናል የጌታ መምጣት ግን ቶሎ እንደሚሆን ማሰብ አለብን፤

ያንቀላፉቱን አንቀድምም የሚለው ስለ አማኞች ትንሳኤና መነጠቅ ነው፤ ያንቀላፉት (የሞቱት) አማኞች አሁን ከጌታ ጋር ስላሉ፤ ደግሞም ከጌታ ጋር አብረው ስለሚመጡ እነሱ በስጋ ትንሳኤ በመነሳት እንደሚቀድሙን ያሳይል፤ ትንሳኤ ማለት የስጋችን በህይወት መዋጥ ማለት ነው፤ በትንሳኤ የተነሳ ስጋ ደግሞ አይሞትም፤

**16.** በዚህ ቁጥር ላይ ጌታ ራሱ የሚለው ጌታ ለሚከተሉትና ስለስሙ መከራለተቀበሉት ምን ያህል ክብር እንዳለው ያሳይል፤ መላዕክቱን ብቻ ልኮ ሳይሆን ራሱ መጥቶ እንደሚቀበለን ያሳያል፤

በትዕዛዝ የሚለው ጌታ ለመላዕቱ ስለሚሰጠው ትዕዛዝ ነው፤ ጌታ ስለ እኛ መላዕክቱን ያዛል፤ ይህ ትዕዛዝ የምናምነው ይዘውን እንዲነጠቁ ነው፤
በመላእክቱም አለቃ ድምፅ ሲል ከጌታ ተቀብሎ መልዕክቱን ወደሌሎች መላዕክቱ ስለሚያስተላልፈው የመላእክቱ አለቃ ነው፤
በእግዚአብሔርም መለከት የሚለው ለሞቱትና በህይወት በምድር ላለነው አማኞች የሚሰጥ የጥሪ ድምፅ ነው፤ መለከት ብዙ አይነት ጥቅም ቢኖረውም እዚህ ጋር ጥሪ የሚሰጥ ነው፤

የጌታ ዳግመኛ ምጣት ለሁሉም ግልፀ በሚሆንበት መንገድ ነው የሚሆነው፤ አንዳንድ ጊዜ የጌታ መምጣት አልፎአል የሚሉ ሰዎች ቢኖሩም ይህ ቃል እንዳንሳሳት ይረዳናል፤ የጌታ መምታት ጩኸት የሞላበት ሁሉ የሚሰማመውና ሁሉ የሚያየው ለአማኞች ክብር የተሞላበት ይሆናል

በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ የሚለው ከላይ ስለተጠቀሱት በጌታ አምነው ስለሞቱት አሁን ከጌታ ጋር ስላሉትና አብረውት ስለሚመጡት ነው፤ ከጌታ ጋር የሚመጣው መንፈሳቸው ሲሆን፤ ይነሣሉ የሚለው በምድር ስላለው ስለስጋቸው ነው፤ በትንሳኤ ስጋቸው ለብሰው ይነሣሉ፤

**17.** ይህ ክፍል የሚነግረው ከጌታ ጋር የሚመጡት ቅዱሳን በምድር ያለውን ስጋቸውን ለብሰው በትንሳኤ ከተነሱ በኋላ እኛ ከእነሱ ጋር ወደ መንግስተ ሰማይ ሊወስደን አየር ላይ የሚጠብቀንን ጌታ ለመገናኘት አብረናቸው እንደምንነጠቅ ነው፤

እንዲሁም ሁል ጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን የሚለው ዋናውን ተስፋችንን ያሳያል፤ የአማኝ መጨረሻ ሞት ሳይሆን በትንሳኤ ተነጥቆ ከጌታ ጋር ለዘላለም መኖር ነው፤ ሞት ለአማኝ ጊዜ ማሳለፍያ እንቅልፍ ነው፤

**18.** ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ፤ አማኝ ሊያዝን ይችላል፤ ጌታን አምነው ስለሞቱ ወገኖች ስናስብ ወይም እኛም እንደምንሞት ስናስብ ሃዘን ሊወረስን ይችላል፤ ነገር ግን ጌታ ዳግመኛ መጥቶ በትንሳኤ ሁላችንን ከሞት አትርፎን ወደ እርሱ እንደሚወስደንና ለዘላለምም ከርሱ ጋር እንደሚያኖረውን ማወቃችን ሊያጽናናን ይገባል፤ አሁን ስለጌታ መከራ መቀበላችን ዋጋ መክፈላችን በከንቱ አይደለም፤ ሞት መጨረሻችን ቢሆን ከንቱ ነበር፤ ነገር ግን ሞት መጨረሻችን አይደለም፤ ስለዚህ አዝነው ያሉ ወገኖችን ስለጌታ መጥቶ ከርሱ ጋር እንድንኖር እኛን እንደሚወስደን በመንገር ልናጽናና ይገባል፤ ሁላችንም ሌላውን ማጽናናት እንችላለን

<u>የጥናቱ ዓላማ:-</u> ጽኑ ተስፋችን የሆነውን የጌታን መምጣት፤ የእማኞችን ትንሳኤና መነጠቅ እንዲሁም ከጌታ ጋር ለዘላለም እንደምንኖር አማኞች እንዲያውቁና በዚህም እውቀት እርስ በርሳችን እንድንጽናና ለማነሳሳት ነው፤

<u>መግቢያ:-</u> ከምዕራፍ አንድ እስከ አራት ቁጥር 12 ድረስ አማኞች በሚቀበሉት መከራ ውስጥም በእምነታቸውና በፍቅራቸው ሊበረቱ እንደሚገባ አይተናል፤ በዚህ ክፍል ደግሞ ጽኑና አጽናኝ ስለሆነው ስለ ወደፊት ተስፋችን እናያለን፤ በ ቁ.13 ሞት እንቅልፍ እንደሆነ ይናገራል፤ ቁ14-17 ስለ ጌታ ዳግመኛ መምጣት፣ አሁን ሞተው ስላሉ አማኞች አብረውት መምጣት፣ ስለ አማኞች ትንሳኤ፣ ስለመነጠቅ እና ከጌታ ጋር ለዘላለም ስለምንኖረው ኑሮ ይናገርና በቁ.18 ይህን እውነት ይዘን እርስ በርሳችንን ልናጽናና እንደሚገባን ያሳየናል፤

<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. ተስፋ እንደሌላቸው የሚለው ስለማን ነው የሚያወራው?

    1.1. ምንስ ማለት ነው?

    1.2. ለምንድን ነው ተስፋ የሌላቸው?

    1.3. አንቀላፍተው ስላሉቱ የሚለው ስለማን ነው የሚናገረው?

2. የጌታ ሞትና ትንሳኤ ጳውሎስ ከዚህ በኋላ ሊናገር ካለው እውነት ጋር እንዴት ነው የሚገናኘው?

በኢየሱስ ያንቀላፉቱ ሲል በኢየሱስ ማንቀላፋት ምን ማለት ነው?
ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል የሚለው ስለማን ነው?

3. በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህንን ነው ሲል ስለሚነገረው እውነት ምን ይነግረናል ወይም የ እግዚአብሔር ቃል መሆኑን ማወቃችን ምን ይጠቅመናል?
ያንቀላፉቱን አንቀድምም የሚለው በምን ስለመቅደም ነው?

4. በቁ.16 ላይ ጌታ ራሱ . . . ከሰማይ ይወርዳልና የሚለው ጌታ ስለኛ ስላለው ክብር ምን ይናገራል?

በትዕዛዝ የሚለው የምን ትዕዛዝ ነው?

በመላእክቱም አለቃ ድምፅ የሚለው ስለምን የሚናገር ድምፅ ነው?

በእግዚአብሔርም መለከት ሲል የመለከቱ አላማ ምንድን ነው?

በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ ሲል የሞቱት በህይወት ካሉት በትንሳኤ የሚቀድሙት ለምን ይመስልሃል? ይህስ ስለ እግዚአብሔር ጻድቅነት ምን ይነግረናል?

5. ቁ.17 ስለ አማኞች መነጠቅ ምን ያስተምራል?

5.1. እንዲሁም ሁል ጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን የሚለው ስላወደፊት ተስፋን ምን ምን ይነግረናል?

6. በቁ.18 መሠረት ማን ነው ማጽናናት የሚችለው?
ማን ነው መጽናናት ያለበት?
የሚያጽናናው ምንድን ነው? ለማጽናናት የምንጠቀመው ምንድን ነው?

መጽናናት የሚያስፈልገን ለምንድን ነው?

መደምደምያ፡ የተሰሎንቄን ሰዎች በመከራ ውስጥ እያሉ ስለጌታ መምጣትና እርሱ ሲመጣ ለእነሱ ስለሚሆንላቸው ነገር ነግሮ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ቃል እንዳጽናናቸው፤ እንዲሁ እኛም በዚህ ቃል ልንጽናና ይገባናል፤ ዛሬ የመጽናኛችን መሠረቱ ምንድን ነው? ስለ ዘላለም ህይወት ስታስብ/ቢ ተስፋ በውስጥህ/ሽ አለ? ደስ ይልሃል/ሻል?

ጥናት ስምንት
ነቅተን እንጠብቅ

የምንባብ ክፍል፡ 1 ተሰ 5፡1-11

የአስተማሪው ማሰታወሻ

**1.**ስለዘመናትና ስለ ወራት የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ሊፈጽማቸው ያሉ ነገሮችን የሚመለከት ነው፤ ከላይ ስለ ጌታ መምጣትና እሱ ሲመጣ ስለሚሆንልን ተስፋ ሲናገር ስለነበር ዘመናትና ወራት ጌታ የሚመጣበትን ጊዜ የሚመለከቱ ናቸው፤ ዘመን ማለት ሰዓትን (ለምሳሌ ዓመተ ምህረት፣ ቀንን ይመለከታል) ወራት የሚለው በተለምዶ ወር የምንለውን ሳይሆን ወቅትን ወይም ሁኔታዎችን ይመለከታል፤ ጌታ የሚመጣበትን ዘመን ማወቅ አይቻልም፤ የሚመጣበት ወራት (ወቅት) ወይም የሚመጣበት ጊዜ ምን እንደሚመስል የተለያዩ ምልክቶችን ጌታ ሰጥቶናል፤

ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈልጋችሁም ያለው ከዚህ በፊት ስለተነገራቸው ነው፤ ጌታ በዚህ ዓመተ ምህረት ይመጣል ባይባልም የሚመጣበት ወቅት ግን ምን እንደሚመስል በጌታ በራሱ ተገልጾአል፤

**2.** የጌታ ቀን የሚለው በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያየ ትርጉም ቢኖረውም እዚህ ክፍል ግን ጌታ ወደዚህ ምድር ዳግመኛ የሚመጣበትና ቅዱሳኑን ይዞ የሚሄድበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው

አጥብቃችሁ አውቃችኋል የተባሉት የጌታ መምጣት እንደ ሌባ ባልታወቀ ጊዜ መሆኑን በአዕምሮአቸው ማወቅ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ማወቃቸውን ይገልጡ ስለነበር ነው፤ በተግባር ማወቃቸው የሚገለጸው ሃሳባቸውን ከምድር ነገር አንስተው ጌታን ቶሎ ይመጣል ብለው ይጠብቁ ስለነበር ነው፤

**3.**ሰላምና ደኅንነት ማለት በምድር ላይ ሰዎች ከሰዎች ሃገር ከሃገር ጋር ያላቸው ህብረት ሰላም የሞላው፤ የተፈጥሮ ችግርን ተቋቁመን እንኖራለን የሚያቅተን ነገር የለም ብለ ማለት ነው

ጥፋት የሚለው የጌታን መምጣት አስቀድሞ የሚሆነው ዓለምን ሁሉ የሚያጠቃ ተፈጥሮአዊና ማህበራው ችግር ነው፤ ለምሳሌ፡ ጦርነት፣ የፍቅር መቀነስ፣ የተፈጥሮ አደጋና የመሳሰሉት

ከቶም አያመልጡም የሚለው የአለም ችግር መፍትሔ እያገኘ የሚሄድ ሳይሆን ነገሮች እየከፉ እንደሚሄዱ ያሳያል፤ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሃገሮች የተፈጥሮን ጥፋት የተቋቋሙ ቢመስላቸውም በመጨረሻው ዘመን ሊቋቋሙት የማይችሉት ችግር እንደሚመጣ ያሳያል

**ቁ.4** ቀኑ የሚለው ጌታ የሚመጣበት ቀን ማለት ነው እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም እዚህ ጋር ጨለማ የሚለው ስይጣንን ያሳይል፤ ጌታን የማያምኑ አሁንም በሰይጣን ግዛት ስር ያሉት በጨለማ ናቸው፤ እነዚህ ሰዎች ጌታ ይመጣል ብለው አያምኑም ስለዚህም አይጠብቁትም፤ ጌታን የሚያምኑ ግን የጌታን መምጣት በመጠባበቅ ስለሚኖሩ ጌታ ሲመጣ ድንገት አይሆንባቸው፤ ምንም እንኳ በዚህ ቀን ይመጣል ማለት ባይቻልም ዛሬም ሊመጣ ይችላል ብሎ ለሚኖር የጌታ መምጣት እንደ ሌባ መምጣት አይሆንበትም

**ቁ.5** የብርሃን ልጆች የሚለው ብርሃን የሆነው የእግዚአብሔር ልጆች ማለት ነው፤ በብርሃን ወይም ግልጥ በሆነ ሁኔታ እንደምንኖር ያሳያል፤ እግዚአብሔር ልናውቅ የሚገባንን ሁሉ ስለነገም ስለዛሬም እንዲሁም ስለትላንት ግለጥ አድርጎ ነግሮናል

የቀንም ልጆች ሲል መልካም የሆነውን ነገር፣ የማያሳፍረውን ነገር፣ ሃጢያት ያልሆነውን ነገር በግልጥ እያደረጉ የሚኖሩ ማለት ነው

**ቁ.6** እንንቃ ማለት አይናችንን ከፍተን የጌታን መምጣት እያሰብን መልካምን ወይም በጎ የሆነውን ነገር ለማድረግ ነቅትን እንኑር ማለት ነው
በመጠን እንኑር ማለት ልቅ አንሁን፣ ራሳችንን እንግዛ ማለት ነው፤
እንደሌሎች አናንቀላፋ ማለት የማያምኑ ሰዎች የጌታን መመጣት ሳይጠባበቁ እንደሚኖሩ እኛም እንደነሱ አንሁን ማለት ነው
**ቁ.7** ሌሊት የቀን ተቃራኒ ነው፤ ቀን መልካም የሆነውን የማያሳፍረውን ነገር የምናደርግበት ግለጥ የሆነ ጊዜ እንደሆነ ሌሊት ሰዎች ተደብቀው ሃጢያትን የሚያደርጉበት ድብቅ የሆነ ጊዜ ነው፤

የሚያንቀላፉ በሌሊት ያንቀላፋሉ የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉ ሲል በመጀመርያ ምድራዊ ስለሆነው ምሽት የሚናገር ነው፤ በርግጥ ለመተኛትም ለመስከርም ሰዎች ሌሊትን ነው የሚጠቀሙት፤ ይህ ምድራዊ ነገር

መንፈሳዊም ትርጉም ተሰጥቶታል፤ ሰዎች ሃጢያትን ለማደረግ ሌሊትን ወይም ስውር ድብቅ የሆነን ምቹ ጊዜ ይጠቀማሉ

**ቁ.8** ይህ ቁጥር የሚነግረን በቀን/በግለጥ መልካምን እያደረግን የምንኖር ሰዎች ስለሆንን በተለይ እምነትን ፍቅርን አና ተስፋችንን አጥብቀን ልንይዝ ይገባል፤

የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር ሲል እምነትና ፍቅር ሲኖሩን እንደጥሩር እንደሚጠብቁን ያሳያል የመዳንን ተስፋ ማለት ከመዳናችን የተነሳ ያገኘው የወደፊት ተስፋ ማለት ነው፤ ይህም ተስፋ በዚህ ክፍል እንዳየነው ከጌታ ጋር ለዘላለም መኖር ነው፤

እንደ ራስ ቁር ማለት ከመዳናችን የተነሳ ያገኘነውን ተስፋ ስንይዝ ረሳችንን(አይምሮአችንን ከጠላት ሽንገላ መጠበቅ እንችላለን ማለት ነው

**ቁ.10** የምንነቃም ብንሆን ማለት በስጋ በዚህ ምድር እሰካለን ድረስ ማለት ነው

የምናንቀላፋም ብንሆን ማለት በስጋ ብንሞትም ማለት ነው

ከእርሱ ጋር አብረን በህይወት እንኖር ዘንድ የሚለው በዚህም ምድር ይሁን በወዲያኛው እግዚአብሔር ለእኛ አንድ አላማ አለው፤ ይህም ከእርሱ ጋር ህብረት እያደረግን እንድንኖር ነው፤

<u>የጥናቱ ዓላማ፡-</u> ጌታ ሲመጣ የሚፈፀመውን ተስፋ አይተው አማኞች ዘሬ በመንፈሳዊ ህይወታቸውና በባህርያቸው ጥንቁቅ ሆነው የጌታን መምጣት እንዲጠባበቁ ለማበረታታት

<u>መግቢያ፡-</u> ባለፈው ጥናት ጌታ እንደሚመጣና ሲመጣ የሞቱትንም በምድር ያሉትንም አማኞች በትንሳኤ ካስነሳ በኋላ ወደ ላይ እንደሚነጥቃቸውና ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንዲኖሩ እንደሚረዳቸው አይተናል፤ በዚህ ጥናት ተሳፋችንን ሊፈፅም ጌታ ሲመጣ ሳይታሰብ እንደሚመጣና ስለዚህም ደግሞ አማኞች በንቃት ሆነን ልንጠብቀው እንደሚገባ እናያለን፤ በንቃት መጠበቅ ማለት 1) መንፈሳዊ ንቃት፡ ይህም በአዕምሮአችን የጌታን መምጣት እያሰብን ስለ እርሱ እያሰብን እየጸለይን መጠባበቅ ነው 2) የባህርይ ንቃት፡ ይህም ጌታ ሲመጣ ሁሉን እንደስራው ስለሚከፍለው በቅድስና ራሳችንን በመግዛት፣ በንስሃ መመላለስ ነው

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በቁ.1 ላይ ዘመናትና ወራት የሚለት የምን ዘመንና ወራት ናቸው?
   ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈልጋችሁም ያላቸው ለምንድን ነው?

2. በቁ.2 ላይ አጥብቃችሁ አውቃችኋል ሲል አጥብቆ ማወቅ ምን ማለት ነው?
   አጥብቀው ያወቁት ምንድን ነው?

3. ሰላምና ደህንነት ሲሉ የሚለው ማንን ነው?

   የምን ሰላምና ደህንነት ነው?

   ያን ጊዜ የሚለው የትኛውን ጊዜ ነው? (ሰላምና ደህንነት ነው ብለው ተዘናግተው የተቀመጡበትን ጊዜ ነው)

   ጥፋት የሚለው ምን ዓይነት ጥፋት ነው?
   
   አያመልጡም የሚለው ከምንድን ነው? ለምንስ ነው የማያመልጡት?

4. በቁ.4 ላይ ቀኑ እንደሌባ የማይደርስባቸው ለምንድን ነው?

በጨላማ አይደላችሁም ሲል ምን ማለት
ነው?

5. የብርሃን ልጆች ማለት ምን ማለት ነው?

የቀን ልጆች ማለት ምን ማለት ነው?

የሌሊትና የጨለማ ልዩነት ምንድን ነው?

6. እንንቃ ሲል ስለምን አይነት መንቃት ነው የሚናገረው?

በመጠን መኖር ምን ማለት ነው?
እንደሌሎች አናንቀላፋ ሲል ሌሎች የሚለው ማንን ነው? ማንቀላፋትስ ምን ማለት ነው?

7. በሌሊት ማንቀላፋት ማለት ምን ማለት ነው?
በሌሊት መስከር ማለት ምን ማለት
ነው?

8. እኛ ከቀን ነን ማለት ምን ማለት ነው?

ከቀን ስለሆንን ምን እናድርግ ይለላል?

እምነትን እንደ ጥሩር መልበስ ምን ማለት ነው?

ፍቅርን እንደ ጥሩር መልበስ ምን ማለት ነው?

የመዳን ተስፋ ማለት ምን ማለት ነው?

በመጠን እንኑር የሚለው ትዕዛዝ በድጋሚ መነገሩ ምን ያስተምራል?

9. በቁ.9 ላይ እግዚአብሔር ለምንድን ነው የመረጠን? አብራራ/ሪ

10. የምንነቃም ብንሆን የምናንቀላፋም ብንሆን ሲል ስለምን ዓይነት መንቃትና ማንቀላፋት ነው የሚያወራው?

በቁ.10 ላይ ክርስቶስ ለምንድን ነው የሞተልን የሚለው?

11. ከተሰጠን ተስፋ የተነሳ በቁ.11 ላይ እርስ በርሳችን ምን እንድናደርግ ታዘናል? አብራራ/ሪ።

መደምደምያ፡ ጌታ እንደሚመጣ ካመንን ይህ እምነታችን በስራ ሊገለጥ ይገባዋልና ተግባራችንና የዕለት ኑሮአችን ጌታ እንደሚመጣ ነው ወይስ ኑሮአችን ከማያምኑት ምንም አይለይም?

ጥናት ዘጠኝ
ሚዛን የጠበቀ ህይወት

የምንባብ ክፍል፡ 1 ተሰ 5፡12-28

የአስተማሪው ማስታወሻ

**ቁ.12-13** የሚደክሙ ማለት የሚሰሩ ወይም የሚታገሉ ማለት ነው
የሚገዙአችሁ ማለት የሚያስተዳድሩአችሁ ማለት እንጂ የሚሰለጥኑባችሁ ወይም የሚበረቱባችሁ ማለት አይደለም
የሚገሥጹአችሁ ማለት በፍቅር ስህተትን ስህተት ብለው የሚነግሩን ማለት ነው እወቁ
ሲል እውቅና ስጡአቸው ማለት ነው
ስለሥራቸው . . . ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ ሲል ለ እኛ የሚደክሙትን እውነትን የሚነግሩን ስንስት የሚመልሱንን ከማንም በላይ ትልቅ ስፍራ በህይወታችን ልንሰጣቸው እንደሚገባ ይናገራል በፍቅር ሲል ይህን ማክበር የምንሰጣቸው ወደናቸው እንጂ ትዕዛዝ እንደሆነ ተሰምቶን መሆን የለበትም

**ቁ.14** ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው ራሳቸው ገዝተው በመጠን የማይኖሩትን የ እግዚአብሔርን ትዕዛዝ የማይታዘዙትን ከሥህተታቸው መመለስ እንዳለብን ያሳያል
ድፍረት የሌላቸውን አጽኑ ሲል በፍርሃት የሚኖሩትን ማንኛውም ከሞተልን ከክርስቶስ የተነሳ ልንፈራው የሚገባ ነገር እንዳሌለ እያሳየን አሁን በፈሩት ነገር ውስጥ መጽናናት እንዲችሉ መርዳት ለደካሞች ትጉላቸው ማለት ራሳቸው መርዳት የማይችሉትን ሰዎች ሁሉ በደከሙበት ነገር መርዳት እንዳለብን ያሳያል
ሰውን ሁሉ ታገሡ ሲል የሚያምኑትን ብቻ ሳይሆን የማያምኑትንም ሁሉ በማንኛውም ነገር በሚፈትኑንና በሚያሳዝኑን ጉዳይ ጌታ በቅርቡ መጥቶ እንደሚገላግለን እያሰብን መታገሥ እንዳለብን ያሳያል

ከቁ**12-13** በረትተው እኛን ስለሚያበረቱ ሰዎች ሲናገር በቁ.14 ላይ ደግሞ ስለደከሙና እኛ ልናበረታቸው ስለሚገባን ሰዎች ይናገራል፤ እንዚህን አይነት ሁለት ጎራ ሰዎች ሁል ጊዜ ያጋጥሙናል፤ አንዱን ይዘን ሌላውን እንድንጥል ሳይሆን ከሁለቱም ጋር መኖር እንዳለብን ታዘናል፤ በቁ.**13** መጨረሻ ላይ እርስ በርሳችሁ በሰላም ኑሩ የሚለው ከኛ በላይ ከበረቱት ጋርና ከኛ በታች ከደከሙት ሰዎች ጋር ተስማምተን እየተጋገዝን መኖር እንዳለብ ይነግረናል

**ቁ.15** ማንም በሌላው ክፉ ፈንታ ማለት አንድ ሰው በኛ ላይ በሚያደርገው ክፉ ምትክ ማለት ነው፤ ክፉ ሲደረግብ ክፉ መመለስ እንደሌለብን ያሳስበናል
ለሁሉም መልካምን ለማድረግ ትጉ ሲል መልካም ለሚያደርጉልን ብቻ ሳይሆን ክፉም ለሚያደርጉል ክፉ በማደረግ ፈንታ መልካምን እንድናደርግ ያዘናል
በዚህ ቁጥር ደግሞ ሌላ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን እንዴት እንዱን ትተን ሌላውን መያዝ እንዳለብን ይነግረናል

**ቁ.16** ሦስተኛ ተቃራኒ ነገሮች ሁሌ መደሰትና ሳያቋርጡ መጸለይ ነው ደስታ ነገሮች እንደፈለግነው ሲሄዱል የምንገልጸው ሲሆን ጸሎት በተለይ በችግር ውስጥ ስንሆን የምናደርገው ነው

**ቁ.17-18** ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ተቃራኑ ነገሮች (የሚያስደስተንና የሚያስጸልየን ነገር ሲመጣ በሁለቱም ጊዜ ልናደርገው የሚገባ ነገር ቢኖር በሁለቱም ውስጥ ስንሆን እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባል

**ቁ19-20** መንፈስን አታጥፉ ሲል መንፈስ ቅዱስን አትቋቋሙ፣ አትከልክሉት ማለት ነው ትንቢትን አትናቁ ማለት እግዚአበሔር በሰዎች የሚናገረውን የትንቢትን ቃል በትዕቢትና በንቀት፣ አይፈጸምም እያልን እንዳንኖር ያዘናል

መንፈስንም እንዳናጠፋ ትንቢትንም እንዳንንቅ ሁሉን መፈተን አለብን  ከመንፈስ ቅዱስ የሆነና ያልሆነውን ትክክለኛ የሆነና ያልሆነውን ትንቢት በእግዚአብሔር ቃል ፈትነን ማወቅ እንችላለን፤ ነገር ግን ይህ ቃሉን በደንብ ማወቅ ይጠይቃል

**ቁ.21-22** መልካምን ያዙ ሲል መልካም የሆነ ነገርን ባህርያችን ባህላችን ወይም የእኛ ልናደርገው እንደሚገባ ሲያሳይ ከማኝኛውም ክፉ ነገር ራቁ ሲል ገና ለገና እግዚአብሔር ከልክሎአል እያልን ሳይሆን ክፉን ነገር ልንርቀው በሃሳባችንም ቢሆን በንግግራችን እንዲሁም በልምዳችን በእኛ ውስጥ እድል ፈንታ እንዳይኖረው ያዘናል
**ቁ.23-24** የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ ማለት በጎ የሆነውን እያስያዘ ክፉ የሆነውን እያስጣለ ያኑራችሁ ማለት ነው

የሚጠራችሁ የታመነ ነው ማለት እንድንቀደስ የጠራን ሊቀድሰን የሚወድና የሚችል የሚያደርገውም አምላክ ነው ማለት ነው

የጥናቱ ዓላማ:- ቅዱሳን ሁሉ እንዴት እርስ በርሳቸውን መምክርና ማነጽ እንደሚችሉ ለማስረዳትና በግልም በጋራም ሚዛኑን የጠበቀ ህይወት ምን እደሚመስል ለማሳየት ነው

መግቢያ:- ባለፈው ጥናት 1 ተሰ 5፡1-11 አይተናል፤ ቁ.11 ላይ እርስ በርሳቸው እንዲመካከሩና እንዲተናነጹ ታዘው ነበር፤ በዚህ ጥናት የምናይው እንዴት እርስ በርሳቸው እንደሚመካከሩና እንደሚተናነጹ እንደታዘዙ ነው፤ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን እንዴት በግልና በጋራ ሚዛን ጠብቀው መኖር እንዳለባቸው እናያለን።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በመካከላችሁ የሚደከሙትን ሲል መድከም የሚለው ምን ማለት ነው?
   የሚገዙአችሁ ማለት ምን ማለት ነው?
   የሚገሥጹአችሁ ሲል ተግሣጽ በዚህ ክፍል ምንድን ነው?
   ታውቁ ሲል ምን ማለት ነው?

ታከብሯቸው ዘንድ ሲል ማንን ስለማክበር ነው የሚናገረው? ማክበርስ ማለት ምን ማለት ነው? በፍቅርአከብሩአቸው ሲልስ ፍቅር መኖሩ ጥቅሙ ምንድን ነው?

2. ያለሥርዓት የሚሄዱትን የሚለው ስለምን አይነት ሰዎች ነው?

   2.1. ያለሥርዓት የሚሄዱትን ምን አድርጉ ይላል?

   2.2.መገሠጽ ምን ማለት ነው? ማንስ ነው መገሠጽ የሚችለው?

   2.3.ድፍረት የሌላቸው የሚለው ስለምን አይነት ድፍረት ነው? እንዴትስ ነው እርዱአቸው የሚለው?

   2.4.ደካሞች የሚላቸው ምን አይነት ድካም ስላላቸው ሰዎች ነው? እንዴትስ ነው እርዱአች የሚለው?

   2.5.ሰውን ሁሉ ታገሡ ሲል ለምንድን ነው ታገሡ የሚለው?

   2.6.በቁ.13 መጨረሻ ላይ አንድ ሰው ከሚበረቱም ከሚደከሙም ሰዎች ጋር ሲኖር ምን ማድረግ እንዳለበት የተጠቀሰው ምንድን ነው? (በሰላም ኑሩ)

3. በቁ15 ላይ የተጠቀሱ ሁለት ተቃራኒ ድርጊቶች ምን ምን ናቸው?

4. በቁ.16 ላይ ሁል ጊዜ ደስ ይበላችሁ የተባሉት ለምንድን ነው?

   4.1. ሳታቋርጡ ጸልዩ የተባሉት ለምንድን ነው?

4.2.በሁሉ አመስግኑ ሲል ሁሉ የሚለው ምን ምንን ያካትታል (ደስ የሚያሰኘንም የሚያስጸልየንም ችግር ሲመጣ)

4.3.በዚህ ክፍል መሰረት የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው?

5. መንፈስን አታጥፉ ሲል ምን ማለቱ ነው?

   5.1. ትንቢትን አትናቁ ሲል ምን ማለቱ ነው?

   5.2. ሁሉን ፈትኑ ሲል ሁሉ የሚለው ምኑን ነው? (መንፈስንም ትንቢትንም)

6. ከቁ.20-22 የተገለጡ ሁለት ትዕዛዛትን ጥቀስ

   6.1. መቀደስ ማለት ምን ማለት ነው?

   6.2. እግዚአብሔር ታማኝ የሆነበት ጉዳይ ምንድን ነው? ታማኝ ነው ሲባልስ ምን ማለት ነው?

7. ጳውሎስ የሚያገለግላቸውን ሰዎች ጸልዩልን ሲል ከሱ ምን ትማራለህ/ሪአለሽ?

8. የተቀደሰ አሳሳም ምን አይነት ነው?

9. ይህ መልእክት ለቅዱሳን ወንድሞች ሁሉ እንዲነበብ በጌታ አምላችኋለሁ(ወይም አደራ እላችኋለሁ) ማለቱ ይህን የተሰሎንቄን መልእክት ሌሎችም ሰዎች እንዲያነቡ ልታነሳሳ/ሺ ሃላፊነት እንዳለብህ/ሽ ይሰማሃል/ሻል?

መደምደምያ:- ተስፋ ያለን ሰዎች ነን ብለን ግን ተስፋ እንደሌላቸው ሰዎች መኖር አቁመን ይልቁንስ ስለተስፋችን ስንል ዛሬ እርስ በርሳችንም ሆነ በግል ህይወታችን ሚዛን የጠበቀ ህይወት እየኖርን ነው? በቃሉ ስህተታችንን ድካማችንን ካየን በኋላ ራሳችንን ለማስተካከል ወስነናል?